ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ዓርብ

83ኛ ዓመት ቁጥር 354 ነሐሴ 24 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)
የሁሉም ባንክ
Bank for all !
የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ !

በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia



# የሶማሊያ አካሄድና ቀጣዩ የኢትዮጵያ የቤት ሥራ

**ሞገስ ፀጋዬ**

**ዜና ትንታኔ**

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በአፍሪካ ቀንድ ወቅታዊ ቀጣናዊ ጉዳይ ላይ ከትናንት በስቲያ መግለጫ አውጥቷል። መግለጫውም በሶማሊያ የአፍሪካ ኅብረት የሽግግር ተልዕኮ (አትሚስ) በቀጣይ የሚኖረው አዲስ የሠላም ተልዕኮ አወቃቀር ሁኔታ በአፍሪካ ቀንድ ቀጣና ላይ አዲስ ስጋት ይዞ መምጣቱ ኢትዮጵያን የሚያሳስብ ሆኗል ይላል፡፡

የአፍሪካ ኅብረት እና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለዚሁ አዲስ ሽግግር እየተዘጋጁ ባሉበት ወቅት፣ ቀጣናው ሊተነበይ ወደማይቻል ፈተና ውስጥ እየገባ ይገኛል የሚለው መግለጫው፤ በሁኔታው ላይ ቀደም ሲል ኢትዮጵያን ጨምሮ በሶማሊያ የአፍሪካ ኅብረት ተልዕኮ ውስጥ ወታደር ያዋጡ አገሮች ተደጋጋሚ ጥሪዎችና አስተያየቶች ትኩረት አልተሰጣቸውም ነው ያለው፡፡

የመከላከያ ሠራዊታችንን መልካም ስምና ዝናን እንዲሁም

የሶማሊያ አካሄድና... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የትራንስፖርት ቢሮ
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION
TRANSPORT BUREAU

ማስታወቂያ

ከ70 ኩንታል በታች የመጫን አቅምና የአዲስ አበባ ኮድ-3 ሰሌዳ ያላችሁ የጭነት አገልግሎት ሰጪ ባለንብረቶች በሙሉ

የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ በአዋጅ 84/2016 በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት በጭነት ትራንስፖርት የንግድና የግል ንግድ ዘርፍ ለተሰማሩ አገልግሎት ሰጪዎች በመስፈርቱ መሰረት የብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ እየሰጠ ይገኛል፡፡

ሆኖም በከተማዋ በተለያዩ ቦታዎች ከ70 ኩንታል ወይም ከ 7 ቶን በታች የመጫን አቅም ኖሯቸው በንግድና በግል ንግድ ዘርፍ የተሰማሩ የአዲስ አበባ ኮድ-3 ሰሌዳ ያላቸው የጭነት ተሽከርካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ ከቢሮው ሳያገኙ አገልግሎቱን ሲሰጡ ይስተዋላል፡፡

በመሆኑም ቢሮው በልዩ ሁኔታ ከነሐሴ 15 ጀምሮ አገልግሎቱን እየሰጠ ሲሆን ባለንብረቶች እስከ መስከረም 10/2017 ዓ.ም ዘወትር ከሰኞ እስከ አርብ ከጠዋቱ 2:30 - 11:30 የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቢሮ መገናኛ ስሪ ኤም ሲቲ ሞል 13ኛ ፎቅ አስፈላጊውን መረጃ በማሟላት አገልግሎቱን ማግኘት እንደምትችሉ ቢሮው በጥብቅ ያሳውቃል፡፡



አቶ ሰውነት አየለ

# ቢሮው ለመጪው በዓል የግብርና ምርቶች በብዛት እንዲገቡ እያደረገ ነው

## - ሁለት ሚሊዮን ሊትር የምግብ ዘይት ለማቅረብ ታቅዷል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- ከመጪው በዓል ጋር ተያይዞ የዋጋ ንረት ለማረጋጋትና የምርት እጥረት እንዳይፈጠር የግብርናና የኢንዱስትሪ ምርቶች በብዛት ወደ መዲናዋ

ቢሮው ለመጪው... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# በሀገራዊ ምክክሩ የሃይማኖት አባቶች ሚና

**መዓዛ ማሞ**

**ዜና ትንታኔ**

ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ከሰኔ 21 ቀን ጀምሮ የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር ምዕራፍ እያከናወነ ነው። በሲዳማ ክልልም ከነሐሴ 22 ጀምሮ የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር መድረክ በሀዋሳ ከተማ እያከናወነ ይገኛል።

በሀዋሳ ከተማ እየተካሄደ በሚገኘው መድረክ እየተሳተፉ ከሚገኙት ከአንድ ሺህ 800 በላይ ባለድርሻ አካላት መካከል የሃይማኖት አባቶች ይገኙበታል።


እንደ ሀገር አብዛኛው ሕዝብ ሃይማኖተኛ በሆነባት ኢትዮጵያ የሃይማኖት አባቶች በሕዝቡ ዘንድ ያላቸው ተቀባይነት ከፍተኛ መሆኑ እሙን ነው። በሀገራዊ ምክክሩ የሃይማኖት አባቶች ሚና ምን መሆን አለበት? ለስኬታማነቱስ እንዴት ይደረግ? በሚሉት ጥያቄዎች ላይ በሲዳማ ክልል እየተደረገ በሚገኘው የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር መድረክ ተሳታፊ የሆኑትን የሃይማኖት አባቶች ጠይቀን ምላሽ ይዘናል።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሲዳማ ሀገረ ስብከት የሰበካ ጉባኤ ማደራጃ መምሪያ ኃላፊ የሆኑት ምክረ ትጉኃን ቀሲስ አማረ ግርማ እንደሚሉት የሃይማኖት አባቶች በምክክሩ ትልቅ ሚና አላቸው።

ምክክሩ ያጣነውን ሠላም ለማምጣት ወሳኝ ነው የሚሉት ምክረ ትጉኃን ቀሲስ አማረ፤ የሃይማኖት አባቶች



ቀሲስ አማረ ግርማ



ቄስ እያሱ ተገኘ



ሼክ ዑመር ቡሽራ

ለሀገር ይጠቅማል የሚሉትን ሀሳብ በማቅረብ እና በንቃት በመሳተፍ ለሠላም መገኘት አስተዋፅዖ ማበርከት እንደሚጠበቅባቸው ይመክራሉ።

በምክክሩ በየቦታው የሚታዩ ጦርነቶች እና ግጭቶች ቢያንስ በተወሰነ መልኩ መፍትሔ ያገኛሉ ብለው ተስፋ እንደሚያደርጉ የሚናገሩት ሊቀ ትጉኃን ቀሲስ አማረ፤ የሃይማኖት አባቶች ለምክክሩ ስኬታማነት ሁሉም የበኩሉን ድርሻ እንዲያበረክት መምከር እንደሚጠበቅባቸውም ያስገነዝባሉ።

ምክክሩ ለሀገር እና ለሕዝብ የሚጠቅም በመሆኑ ተሳክቶ የሚጠበቀውን ሠላም እንዲያመጣ የሃይማኖት አባቶች በቅንነት የምንችለውን ሁሉ ለማድረግ መጣር አለብንም ይላሉ።

የሲዳማ ክልል የሑላማ ምክር ቤት ምክትል ሰብሳቢ የሆኑት ሼክ ዑመር ቡሽራ በበኩላቸው እንደሚሉት፤ ሃገራዊ ምክክሩ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሊደግፈው እና ከጎኑ ሊቆም የሚገባው ሀሳብ ነው።

ሠላም በእስልምና እምነት ውስጥ ቅድሚያ የሚሰጠው መሆኑን የሚገልጹት ሼክ ዑመር፤ እንደ ሃይማኖት አባት ለምክክሩ ስኬት የበኩላቸውን አስተዋፅዖ ለማበርከት ሁሌም ዝግጁ መሆናቸውን ይናገራሉ።

ሀገራዊ ምክክሩን በስኬት ማጠናቀቅ ከተቻለ ኢትዮጵያ ከግጭት ወጥታ ሠላም ታገኛለች የሚሉት

በሀገራዊ ምክክሩ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

ኤኤምጂ ብረታ ብረት ፋብሪካ
AMG Steel Factory
Tel:- 0940 505050 – 0940 606060 – 0940 909090 – 0940 808080 -0920 656565

# በከተማዋ የሚካሄዱ ክስተቶችን በደኅንነት ካሜራዎች የመያዝና የመከታተል አቅም ተፈጥሯል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

ሀዋሳ፡- በሀዋሳ ከተማ የትኛውንም ክስተት በደኅንነት ካሜራዎች በሚገባ የመያዝና የመከታተል አቅም እንደተፈጠረ የሀዋሳ ከተማ ከንቲባ አቶ መኩሪያ ማርሻዬ ገለፁ።

የሀዋሳ ከተማ ከንቲባ አቶ መኩሪያ ማርሻዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ እንደገለፁት፤ ሀዋሳ አሁን ላይ በደኅንነት ካሜራዎች የምትጠበቅ ከተማ ናት። ይህንንም ይበልጥ ለማጠናከር በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ነው።

ከዚህ ውስጥ አንዱ ከ450 በላይ የንግድ ተቋማት የደኅንነት ካሜራዎችን እንዲገጥሙ ተደርጓል ያሉት ከንቲባ መኩሪያ፤ ይህንንም ከዋናው የመረጃ ማስቀመጫ ቋት ጋር የማስተሳሰር ሥራ እየተሠራ እንደሆነ ተናግረዋል።

በእነዚህ ሥራዎች በሀዋሳ ከተማ የትኛውንም ክስተት በደኅንነት ካሜራዎች በሚገባ የመያዝና የመከታተል አቅም መፈጠሩን ገልፀዋል።

በከተማዋ ድንገተኛ ችግር ከተከሰተ በቅርበት የሚደርሱ ከ40 በላይ የፖሊስ የማቆያ ቦታዎች መኖራቸውን የተናገሩት ከንቲባ መኩሪያ፤ በፖሊስ ማቆያ ቦታዎች የደኅንነት ካሜራ የተገጠመ ሲሆን ከአንዱ የፖሊስ ማቆያ ወደ ሌላኛው መረጃዎች በፍጥነት እንደሚተላለፉም ነው የገለፁት።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ ሠላማዊት ካሣ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የአፍሪካ የከተሞች ፎረምን ከነሐሴ 29 ጀምሮ ታስተናግዳለች። በመድረኩ ከተሞች ልምዶቻቸውን የሚያካፍሉ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ የሀዋሳ ከተማ እንደምትገኝ ተናግረዋል።



ከተሞቻችን በዚህ ብዙ ልምዶችን ከማካፈል ባለፈ ከሌሎች ሀገራት ተሞክሮ ሊወስዱ ይገባል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታ ሠላማዊት፤ የሀዋሳ ከተማ የኮሪደር ልማት በጅማሮ ደረጃ ላይ ቢሆንም እስከ አሁን ባለው የሥራ ሂደት ውስጥ ከተማዋን የሚገልፁ ትልልቅ ነገሮች በፎረሙ ይቀርባሉ ተብሎ ይጠበቃል ብለዋል።

ከተሞች የከተማ ነዋሪዎች ፍላጎት እና የሚያነሷቸውን ጥያቄዎች መመለስ እንዲችሉ ራሳቸውን በየጊዜው ማሻሻል ይኖርባቸዋል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ አዲስ አበባ ላይ የተጀመረው የኮሪደር ልማት በርካታ ውጤቶችን ያስመዘገበ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ የሥራ ዕድሎችን የፈጠረ እንዲሁም የከተማዋን ገፅታ በአጭር ጊዜ ውስጥ መቀየር ያስቻለ ትልቅ ፕሮጀክት መሆኑንም ገልፀዋል።

ይህንን ፕሮጀክት በሁሉም ክልሎች በተለይ ብዙ ነዋሪዎች ያሉባቸውና አቅም ያላቸው ከተሞች ላይ እንዲሠራ በስፋት እቅድ ተይዞ ወደ ሥራ መገባቱን አብራርተዋል፡፡

በዚህ መነሻነት የኮሪደር ልማት በሀዋሳ ከተማ የተጀመረ ሲሆን በርካታ እቅዶችም በሂደት ላይ እንደሆኑ ተናግረዋል።

በመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስተባባሪነት የመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች በሀዋሳ ከተማ የመስክ ምልከታ አድርገዋል።

በመስክ ምልከታው የሀዋሳ ከተማ የኮርደሪ ልማት በሁለት መልኩ ተግባራዊ የሚደረግ እንደሆነ የተገለፀ ሲሆን የመጀመሪያው የማስፋፊያ አካባቢ ላይ ተግባራዊ የሚደረግ ሆኖ ሥራውም 10 መንገዶችን 35 ኪሎ ሜትር የሚሸፍን ይሆናል።

ሁለተኛው በመሐል ከተማ ነባር መንገዶችን ደረጃ የማሻሻል ሥራ በሦስት መንገዶች ላይ ተግባራዊ የሚደረግ ሆኖ ከአምስት ነጥብ ሰባት በላይ ኪሎ ሜትር የሚሸፍን ነው።

ይህም በጥናት የተለዩ ከሳውዝ ስፕሪንግ እስከ ኃይሌ ሪዞርት ያለው የሚያካልል ሲሆን በዚህም የሻፌታ አደባባይ ድረስ ያለው በ50 እና 40 ሜትር ስፋት ያለው ሦስት ነጥብ ሰባት ኪሎ ሜትሮች ያህል መንገድ ግንባታ የሚከናወንበት ነው።



አቶ ዓሊ ይማም

# ዞኑ የሕዝቡን የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች ለመመለስ በትኩረት እየሠራ ነው

**ማሕሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በበጀት ዓመቱ የሕዝቡን የልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን ለመመለስ ብሎም የዞኑን ሠላም ለማረጋገጥ በትኩረት እየሠራ እንደሚገኝ የደቡብ ወሎ ዞን አስታወቀ፡፡

የደቡብ ወሎ ዞን ምክትል ዋና አስተዳዳሪ አቶ ዓሊ ይማም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዞኑ ለተከታታይ ዓመታት በተለያዩ ግጭቶች ውስጥ በመቆየቱ የታቀዱ የልማት እቅዶች በተሟላ መንገድ መፈጸም ሳይቻል ቆይቷል፡፡

በተያዘው በጀት ዓመት ባለፉት ዓመታት የተከሰቱ ጉድለቶች ለማካካስ የሚያስችል የቁጭት እቅድ በማቀድ የዞኑን ሠላም የማረጋገጥ እንዲሁም የሕዝቡን የመልካም አስተዳደርና የልማት ጥያቄዎችን ለመመለስ ይሠራል ብለዋል፡፡

በመሆኑም በዞኑ ከፀጥታ ሥራው ጎን ለጎን የልማት እና የመልካም አስተዳደር ሥራው በትኩረት እንሠራለን ያሉት ኃላፊው፤ ይህም በሁሉም መስክ አበረታችና ለቀጣይም በእርሾነት ሊያገለግሉ የሚችሉ ሥራዎችን ለማከናወን ያስችላል ሲሉ ገልጸዋል፡፡ ሕዝቡንም ተሳታፊ በማድረግ የሠላም ካውንስሉን አጠናክሮ በሠላም የሚያልቀውን በሠላም የመጨረስ፤ ከዚያ ባሻገር ያሉትን የሕግ ማስከበርን በማጠናከር ወደተሟላ ሠላም ለመምጣት ይሠራል ብለዋል፡፡

በፀጥታ ችግሩ ምክንያት የተፈጠረውን የመዋቅር መላላት እና የአመራር አደረጃጀት ክፍተትን ከዞን እስከ ቀበሌ ድረስ የማጠናከር ሥራ እንደሚሠራ አብራርተዋል፡፡ በዚህም የኅብረተሰብን የመልካም አስተዳደር ጥያቄ ምላሽ የሚፈታ አመራር እና የአገልግሎት አሰጣጥ የሚሳለጥበት ሁኔታ መፍጠር የሚያስችል መሆኑን አቶ ዓሊ አስታውቀዋል፡፡

በተጨማሪም በ2017 በጀት ዓመት የተለጠጠ የልማትና የመልካም አስተዳደር ተግባርን ያለፈውን ሊያካክስ በሚችል መልኩ በሁሉም ተቋማት ላይ በተለይም በግብርና፣ ጤና፣ ሰው ሀብት፣ ሥራ ዕድል ፈጠራ እና የኑሮ ግሽበትን ለማስተካከል በትኩረት ይሠራል ብለዋል፡፡

አቶ ዓሊ እንደገለጹት፤ ዞኑ ባለፈው የ2016 በጀት ዓመት ከፀጥታ ሥራው ጎን ለጎን የልማትና መልካም አስተዳደር ሥራ አኳያ ከወቅታዊ የፀጥታ ችግር አኳያ ያለው አፈጻጸም በተወሰነ መልኩ የሕዝቡን ጥያቄ ምላሽ የሰጠ ነው፡፡

ከነዚህም ለከተሞች እድገትና እንቅስቃሴ ወሳኝ ሚና በሚጫወተው የመንገድ መሠረተ ልማት በዓመቱ 24 ኪ.ሜትር መንገድ ሥራ፣ አንድ ሺህ 054 ኪ.ሜትር የመንገድ ጥገና፣ ሦስት ተንጠልጣይ ድልድዮች እንዲሁም አንድ ኮንክሪት ድልድይ አፈፃፀማቸውን ከ70 በመቶ በላይ ማድረስ ተችሏል ብለዋል፡፡

እንዲሁም ቀደም ሲል የተጀመሩ 10 ፕሮጀክቶች ማጠናቀቅ መቻሉን አብራርተዋል፡፡ የዞኑን ነዋሪዎች ንፁሕ የመጠጥ ውሀ ተጠቃሚ ከማድረግ አኳያ 323 አዲስ የውሃ ተቋማት ተገንብተው ወደ ሥራ የገቡ መሆኑን ጠቅሰው፤ ሁለት ሺህ 800 ደግሞ የጥገና ሥራ ተሠርቶ ጥቅም በመስጠት ላይ ይገኛሉ ብለዋል፡፡

በዚህም በአጠቃላይ ከ123 ሺህ በላይ የኅብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ በማድረግ ንፁሕ የመጠጥ ውሃ ሽፋኑን ከ68 በመቶ በላይ ማድረስ መቻሉን አስታውቀዋል፡፡ እንዲሁም የትምህርትን ተደራሽ ለማድረግ ባለፈው በጀት ዓመት 509 ሺህ 690 ያህል ተማሪዎች የተመዘገቡ ሲሆን 79 በመቶ የሚሆኑት ዓመቱን በትምህርት ያሳለፉ መሆናቸውን አቶ ዓሊ ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም በዞኑ የጤና አገልግሎት በማሻሻል እናቶች ወደ ጤና ተቋም መጥተው እንዲወልዱና ክትትል በማድረግ በኩል ከ103 ሺህ በላይ እናቶችን ተደራሽ በማድረግ 78 ሺህ 759 ያህሉ በጤና ተቋም ወልደዋል ብለዋል፡፡ በዓመቱ 439 ሺህ 767 ያህል የጤና መድኅን አገልግሎትን አባላት እና 586 ሺህ በላይ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል ብለዋል፡፡ የዞኑን ኢንቨስትመንት ለማሳደግም በበጀት ዓመቱ ለ4 ባለሀብቶች መሬት መስጠት መቻሉን አብራርተዋል።

# ፈውስ የሚሹት የአጥንት ሕክምና ተቃርኖዎች

**ነፃነት ዓለሙ**

**ዜና ትንታኔ**

የዓለም ጤና ድርጅት መረጃ እንደሚያሳየው ዓለም ላይ ከሚመዘገበው ሞት 10 በመቶው በአደጋ ምክንያት የሚከሰት ነው፡፡ ይህም ተላላፊ የሚባሉት ቲቢ፣ የወባ በሽታ እና ኤችአይቪ ኤድስ ተደምረው ከሚያደርሱት የሞት ብዛት 32 በመቶ ይጨምራል፡፡

በኢትዮጵያ ያለውን ሁኔታ ስንመለከት ተላላፊ በሽታዎች በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች እንዳሉ ሆነው ተላላፊ ያልሆኑ እንደ ስኳር፣ ደምግፊትና ካንሰር ያሉ በሽታዎች እየጨመሩ መሆኑን የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልፃሉ፡፡ ከእነዚህ ውጪ ደግሞ ትልቅ የሀገሪቱ ችግር የሆነው ድንገተኛ አደጋ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ በድንገተኛ አደጋ ምክንያት ከሚከሰቱ ሞቶች 85 በመቶው ሕክምና ለማግኘት በመዘግየት እንደሆነም ባለሙያዎቹ ይገልፃሉ፡፡ ለዚህም ወደ ሆስፒታል ሲላኩ መዘግየት፣ ትራንስፖርት ማጣት፣ ገንዘብ ማጣት እንዲሁም ወደ ባሕላዊ ሕክምና መሄድን እንደምክንያት ይጠቀሳሉ፡፡

የኢትዮጵያ የአጥንትና አደጋዎች ሕክምና ባለሙያዎች ማኅበር በዘመናዊ የአጥንት እና መገጣጠሚያ ሕክምና መስፋፋት እና በባሕላዊ ሕክምና ምክንያት የሚከሰት ውስብስብ የጤና ችግር መካከል የማይገናኝ ተቃርኖ አለ ይላል፡፡ ማኅበሩ በዚህ ምክንያት ቦሳድ የሚባል የጥናት ቡድን መሥርቶ በዘርፉ ያለውን ችግር ለማጥናት መነሻ እንደሆነው የማኅበሩ ፕሬዚዳንት ዶክተር ኤፍሬም ገብረሐና ይገልፃሉ፡፡

ከ10 ዓመት በፊት በጥቁር አንበሳ ብቻ ይሰጥ የነበረው የአጥንት ሕክምና ትምህርት አሁን ላይ በአሥር የተለያዩ ተቋማት ውስጥ እየተሰጠ ይገኛል የሚሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ያኔ ከሰባ የማይበልጡት የአጥንትና የመገጣጠሚያ ሐኪሞች አሁን ላይ 627 መድረሳቸውንም ይገልፃሉ። ነገር ግን በእነዚህ 10 ዓመታት ውስጥ የአጥንት ሕክምና እንደመስፋፋቱ ከባሕላዊ የአጥንት ሕክምና ጋር ተያይዘው የሚመጡ ውስብስብ የጤና ችግሮች መቀነስ ሲገባቸው በተቃራኒው እየጨመሩ ይገኛሉ ባይ ናቸው፡፡

እንደ ፕሬዚዳንቱ ገለፃ፤ ዘመናዊው ሕክምና አሁን የደረሰበት ደረጃ በቂ ነው ባይባልም አሁን የደረሰበት ደረጃ ግን ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ ስለሆነም አሁን ዘመናዊነትን ለመላበስ ሙከራ ካልጀመርን በዓመታት ሂደት ውስጥ ከዚህ የከፋ ጉዳት ሊደርስ ይችላል ይላሉ፡፡

ዶክተር ኤፍሬም እንደሚሉት ቀላል የሚባል ጉዳት ይደርስና ባሕላዊ ሕክምና ሄደው በጣም አጥብቀው ታስረው፣ ታጅለውና ታሽገው ጉዳቱ የደረሰበት አካላቸው እስከመበስበስ ደርሶ ወደ ሆስፒታል የሚመጡ ታካሚዎች በየቀኑ የሚያዩት ችግር መሆኑን ይገልፃሉ፡፡

እንደ እርሳቸው አባባል ልባቸውን ሰብሮ ለዚህ ጥናት ያነሳሳቸው የተለያዩ ዘግናኝ ጉዳቶች አሉ፡፡ ከመታሰርና ከመታሸግ ጋር በተያያዘ እግሩ በስብሶ የመጣ ሕፃን ልጅ ወደ ኦፐሬሽን ክፍል በሚሄድበት ጊዜ እግሩ ቤተሰቦቹ ፊት የወደቀበትን አጋጣሚ አንስተዋል፡፡

በጤና ሚኒስቴር የፖሊሲ ምርምርና ስትራቴጂ ጉዳዮች ኃላፊ ዶክተር እንደገና አበበ በበኩላቸው፤ ባሕላዊ የአጥንት ሕክምና ላይ የሚሠሩ ሰዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ስብራትንና ውልቃትን በማከም ረዥም ታሪክ ያላቸው መሆናቸውንና በልምድ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ያልተሰነደ እውቀት እንዳላቸው ይገልፃሉ፡፡

ምርምሮቹም የተሠሩት እነዚህን ሰዎች ለመገሰፅ ወይም ለመግፋት ሳይሆን ወደ ተሻለ ልምድ፣ እውቀት እንዲሁም ሳይንሳዊ መንገድ እንዲመጡ ለማድረግ ስለሆነ ጤና ሚኒስቴር ምርምሩን ይደግፋል፤ የዘርፉን አካላት በማስተባበርም በጉዳዩ ላይ ለመሥራት ይሞክራል ይላሉ፡፡

አንዱን ጥሎ አንዱን አንጠልጥሎ መሄድ ስለማይቻልና በጤና አገልግሎት ደረጃ የሚፈለገው የሁላችንንም ርብርብ በመሆኑ ተከታታይ ምርምሮች፣ ውይይቶች እና መረጃዎች ያለውን ሁኔታ ፈር እንዲይዝና ወደ ሳይንስ እንዲጠጋ ያስችላል ሲሉም ይገልፃሉ፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ሁሉም ቦታዎች ተመሳሳይ የሆኑ ልምምዶች መኖራቸው፣ ዘመናዊ ሕክምና ባለባቸው ሁሉም ቦታዎች ቀድመን መከላከል የምንችላቸው የአካል ማጣት፣ ቋሚ አካል ጉዳተኝነት እንዲሁም ሞት መመዝገብ መቻሉ፣ የችግሩ መፍቻ የብዙ አካላትን ርብርብ መጠየቁን እንደሚያሳይ ያስረዳሉ፡፡

እንደ አንድ ኃላፊነት የሚሰማው ዜጋ ምርምሩ ወደሚመለከታቸው አካላት ደርሶ ገጠር አካባቢ ለሚኖሩ ሰዎች ሕክምናን ለማዳረስ ይቻል ዘንድ ምርምሩ ማስፈለጉን የገለፁት ደግሞ በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ መምህር



የሆኑት ዶክተር መንግሥቱ ገ/ዮሐንስ ናቸው፡፡

ጥናቱ ከአዋቂዎች በበለጠ ሕፃናት ተጋላጭ መሆናቸውን እንደሚያሳይም የሚገልጹት ዶክተር መንግሥቱ፤ በአብዛኛው አዋቂዎች በመኪና እና በሌሎች አደጋዎች ምክንያት የችግሩ ተጋላጭ ሲሆኑ ሕፃናት ደግሞ በመውደቅ አደጋ እንደሚደርስባቸው ጥናቱ እንደሚያሳይ ይጠቅሳሉ፡፡

በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሕክምና ኮሌጅ ኅብረተሰብ ጤና ክፍል መምህር የሆኑት ፕሮፌሰር ፈንቴ አምባው እንደሚሉት ወጌሻ የሆኑ ሰዎች አብዛኞቹ ከቤተሰብ ወርሰው በልምድ ነው የሚሠሩት፡፡

አንዳንዶች እንስሳት ላይ ሞክረው ስለተሳካላቸው አንዳንዶች በአጋጣሚ ሌሎች ደግሞ የልምድ አዋላጅ ስለነበሩ ይህንንም ብትሞክረው ሲባሉ በዛው የቀጠሉ መሆናቸውን ጥናቱ እንደሚያሳይ ያብራራሉ፡፡

ለውጥ መምጣት ካለበት ግለሰባዊ ሳይሆን ማኅበረሰባዊ መሆን አለበት ማኅበረሰባዊ ለውጥ ደግሞ ግንዛቤ ይፈልጋልም ሲሉ ያስገነዝባሉ፡፡

ወጌሻ መሆን መስፈርት ስለማይጠይቅ ያለእውቀትም እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ በማኅበረሰብ ብቻ ሳይሆን በፖሊሲ ደረጃ መሠራት እንዳለበት ይጠቁማሉ፡፡

ባሕላዊ ወጌሻዎቹን ማሠልጠን፣ የሚችሉትንና የማይችሉትን መለየት፣ እንዲሁም ተጠያቂነት እንዲኖር ማድረግ መቻል እንዳለበትም ያብራራሉ፡፡ የማይችሉትን ነገር እንኳን ወደ ዘመናዊ ሕክምና የማይልኩበት ሁኔታ እንዳለና እንዲደረግላቸው የሚፈልጉትን ሲጠየቁ የቁሳቁስ ችግር ብቻ እንዲደገፉ መጠየቃቸውን ጥናቱ ያሳያል ይላሉ፡፡



ኢንጂነር ወንድሙ ሴታ

# በመንገድ ልማት የሕዝቡን ዘላቂ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ትኩረት ይሰጣል

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- ለመንገድ ፕሮጀክቶች መዘግየት መንስኤ የሆኑ የግዥ፣ የፕሮጀክት ማኔጅመንት እና የዲዛይን ሂደቶች ላይ ያሉ ችግሮችን በመፍታት የሕዝቡን ዘላቂ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ትኩረት እንደሚሰጥ የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ገለጸ፡፡

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ኢንጂነር ወንድሙ ሴታ እንደገለጹት፤ ጥራትን ከማረጋገጥ አንጻር ግዢ፣ ዲዛይን፣ የጥራት ቁጥጥር እና ኮንትራት አስተዳደር ላይ ያሉ ተግዳሮቶችን በመፍታት የሕዝቡን ዘላቂ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ይገባል፡፡

የግንባታው ዘርፍ ለመንገድና ቤቶች ልማት ከፍተኛ አስተዋፅዖ እያደረገ እንደሚገኝ እና መንግሥት በየዓመቱ ለዘርፉ ከ70 እስከ 80 ቢሊዮን ብር እየመደበ እንደሚገኝም አመልክተዋል፡፡

በመንገድ ዘርፍ የሕዝቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣ በቂ የመንገድ መሠረተ ልማት ማስፋፋትና ተደራሽነትን ማስፈን ይጠበቃል ያሉት ኢንጂነር ወንድሙ፤ ለትግበራው የበለጠ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት፣ ተገቢ ሀብትም መመደብ ይገባል ብለዋል፡፡ ያለውን ውስን ሃብት ለላቀ ጥቅም ማዋል የሚቻለው ዘርፉ በጥናት እና ምርምር መደገፍ ሲችል መሆኑንም አንስተዋል፡፡

ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ መጠናቀቅ፣ ረጅም ጊዜ እንዲያገለግሉም ጥራታቸውን በጠበቀ መልኩ መገንባት አለባቸው ያሉት ኢንጂነር ወንድሙ፤ ሥራዎቹን በምርምር እንዲደገፉ በማድረግ የሕዝቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ እንደሚገባም ነው የተናገሩት፡፡

ለመንገድ ፕሮጀክቶች መዘግየት መንስኤ እየሆኑ የሚገኙትን የግዥ፣ የፕሮጀክት ማኔጅመንት እና የዲዛይን ሂደት ላይ ያሉ ችግሮችን በጥናት በመለየት ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመሥራት መፍታት እንደሚገባም ነው የጠቆሙት፡፡

ለመንገድ ልማት የሚመደበው ሃብትም የመንገድ ዘርፉ የተሻለ አፈጻጸም እንዲኖረው ለማድረግና ለምርምር ሂደቱ ጉልህ አስተዋፅዖ እንደሚኖረውም ነው የጠቆሙት፡፡

ይሁን እንጂ አሁን በተያዘላቸው ጊዜ የሚጠናቀቁ የመንገድ ፕሮጀክቶች 32 በመቶ አካባቢ ብቻ መሆናቸውን ጠቁመው፤ ፕሮጀክቶችን በወቅቱ ከማጠናቀቅ አንጻር ብዙ የሚቀር ሥራ እንዳለም ነው የተናገሩት፡፡

ፕሮጀክቶቹ የሚዘገዩበት ጊዜም በአማካኝ 45 በመቶ አካባቢ መሆኑን አመላክተው፤ የምሥራቅ አፍሪካ 22 በመቶ፣ የዓለም አቀፍ ተሞክሮው ደግሞ 10 በመቶ አካባቢ መሆኑን በመጥቀስ ብዙ የቤት ሥራ እንደሚቀር ተናግረዋል፡፡

መንገዶች ከፍተኛ ሃብት ወጥቶባቸው ተገንብተው ረጅም ጊዜ ማገልገል እንዳለባቸውና በቀጣይም ጥራታቸውን የጠበቁ መንገዶች እንዲገነቡ ትኩረት እንደሚሰጥ ገልጸዋል፡፡ ኅብረተሰቡን በሁሉም አካባቢ ፍትሐዊ ተጠቃሚ ለማድረግ የ10 ዓመት እቅድ መውጣቱን አንስተው፣ በቀጣይ ዓመታት እኩል ተጠቃሚነትን መሠረት አድርጎ በወጣ መስፈርት መሠረት የሚገነቡ የመንገድ መሠረተ ልማቶች ተለይተዋል ብለዋል፡፡

ዘርፉ ለሀገር ውስጥ አጠቃላይ ምርት (ጂዲፒ)፣ ለሥራ ዕድል ፈጠራ፣ ለዘላቂ ምጣኔ ሀብት እድገት ያለው ድርሻ ወሳኝ እና ከፍተኛ መሆኑንም ያመላከቱት ሚኒስትር ዴኤታው፤ መንግሥት ለዘርፉ ልዩ ትኩረት በመስጠቱ የመንገድ ሽፋንና ተደራሽነት እያደገ እንደሚገኝም ነው የጠቆሙት፡፡

የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ምክትል ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ሐሩት ዮሐንስ በበኩላቸው፤ የመንገድ ግንባታ ጥራት፣ የፕሮጀክት አስተዳደርና አፈጻጸምን ለማሻሻል ጥናትና ምርምሮችን በመተግበር እየተሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

# በአየር መንገዱ ውስጥ የሚከሰቱ ጨዋነት የጎደላቸው ተግባራት በሕግ አግባብ ይታረማሉ

አማን ረሺድ

አዲስ አበባ፡- በአየር መንገዱ ውስጥ የሚከሰቱ ጨዋነት የጎደላቸው ተግባራት የአየር መንገዱን ስም የሚያጎድፉ በመሆኑ ሊታረሙ እንደሚገባ የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን አስታወቀ።

ባለሥልጣኑ የአየር ትራንስፖርት የሥራ ኃላፊዎች የአየር መጓጓዣ ተሳፋሪ መንገደኞች ሊተገብሯቸው የሚገቡ የሥነምግባር ግዴታዎችን አስመልክቶ በትናንትናው ዕለት ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥቷል፡፡

በባለሥልጣኑ የሴኪዩሪቲና ፋሲሊቴሽን ዳይሬክተር አቶ ደበበ ግርማ በመግለጫው እንዳሉት፤ በአውሮፕላኖች ውስጥ አልፎ አልፎ የሚከሰቱ ጨዋነት የጎደላቸው ባሕሪያት የአየር መንገዱን መልካም ስምና ዝና የሚያጎድፉ ናቸው፡፡

የአቪዬሽን ዘርፍ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠይቅ በመሆኑ ተሳፋሪዎች ከበረራ ደኅንነት አንጻር ለሕግና ደንቦች ተገዢ ሊሆኑ ይገባል ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ የዓለም አቀፉ የሲቪል አቪዬሽን ድርጅት መሥራችና የሲቪል አቪዬሽን ስምምነት ፈራሚ መሆኗን ገልጸው፤ በአውሮፕላን ውስጥ የሚፈጸሙ ሕገወጥ ተግባራት በሕግ አግባብ ይታረማሉ ብለዋል።

አውሮፕላኖች መንገደኞችን ስለጫኑ ብቻ በረራ አያደርጉም ያሉት ዳይሬክተሩ ከሁሉም ነገር በፊት ቅድሚያ ለደኅንነት ይሰጣል ብለዋል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ የአገልግሎት ከፍታውን በጠበቀ መንገድ ለማስቀጠል ለአቪዬሽን ደኅንነት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ ኅብረተሰቡ ስለአቪዬሽን ሕጎች ግንዛቤ እንዲኖረው ባለሥልጣኑ በተለያዩ መንገዶች ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራዎችን እያከናወነ እንደሚገኝ ገልጸዋል።



ፎቶ ሀዲስ አብርሀ

ከመንገደኞቹ የሚነሱ ቅሬታዎችን ለማረም ባለሥልጣኑ ክፍተቶችን ለመቅረፍ የሚያስችሉ የአሠራር ሥርዓቶችን እየተዘረጋ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድን ገጽታን ለማበላሸት የተለያዩ ዘመቻዎች እየተካሄዱ በመሆናቸው ኢትዮጵያውያን ድርጊቱን መከላከል እንደሚገባቸው አስረድተዋል።

ባለሥልጣኑ ከሚያከናውናቸው ዐበይት ተግባራት መካከል የበረራ ደኅንነትን ለማረጋገጥ የሚደረጉ ዘርፈ ብዙ የበረራ ቁጥጥር ሥራዎች አንዱና ዋነኛው በመሆኑ የበረራ ደኅንነትን ማረጋገጥ የአየር መንገዶች ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን የመንገደኞች ጭምር እንደሆነ አመላክተዋል፡፡

የቁጥጥር ሥራዎች ዓለም አቀፍ አሠራርን መሠረት ያደረጉ እና የዓለም አቀፉ የሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ባስቀመጣቸው መስፈርቶችና ስታንዳርዶች የሚከናወኑ ናቸው፡፡ አየር መንገዶችም በጥንቃቄ ሊተገብሯቸው የሚገቡ አሠራሮችን ሲሆኑ የቁጥጥር ሥርዓቱ ዋንኛ ዓላማም የበረራ ደኅንነትን በማረጋገጥ የተሳለጠ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት እንዲኖር ማስቻል ነው ብለዋል፡፡

የአውሮፕላን ምዝገባና የበረራ ብቃት ማረጋገጥ ቺፍ ኢንስቴክተር አቶ አሸናፊ መኮንን በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ የዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ያስቀመጣቸው ከ12 ሺህ በላይ ስታንዳርዶችን በማሟላት ተጠቃሽ ሀገር መሆኗን ተናግረዋል።

የመመዘኛዎቹ ዋና ዓላማ ደኅንነቱ የተጠበቀ የአየር ትራንስፖርት ማረጋገጥ መሆኑን ጠቅሰው፤ ባለሥልጣኑ የአየር ኦፕሬተር የሆነውን ሰው የመገምገም፣ የማረጋገጥ፣ የመቆጣጠር የአቪዬሽን ደንብ መዘርጋቱን ገልጸዋል።




# የሀገሪቱን የንግድ ሥርዓት ለማዘመን የግሉ ዘርፍ ከመንግሥት ጋር በትብብር ሊሠራ ይገባል

## - ለ11 ከፍተኛ የኢትዮጵያ ምርት ተቀባይ ሀገራት እውቅና ተሰጠ

ዳግማዊት አበበና ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- የሀገሪቱን የንግድ ሥርዓት ለማዘመን የግሉ ዘርፍ ከመንግሥት ጋር በትብብር እንዲሠሩ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ተመስገን ጥሩነህ ጥሪ አቀረቡ። 11 ለሚሆኑ ከፍተኛ የኢትዮጵያ ምርት ተቀባይ ሀገራት እውቅና ተሰጥቷል።

4ኛው ሀገራዊ የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ የጋራ ምክክር መድረክ በትናንትናው እለት የተካሄደ ሲሆን ከነሐሴ 19 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ ሲካሄድ የቆየው "የኢትዮጵያን ይግዙ" ልዩ የንግድ ሳምንት ኤግዚቢሽንና ባዛር የማጠቃለያ መርሐግብርም በእለቱ ተካሂዷል፡፡

በመድረኩ ንግግር ያደረጉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ተመስገን ጥሩነህ እንደገለጹት፤ መንግሥት የግሉ ዘርፍ የኢኮኖሚው መሪና አንቀሳቃሽ እንዲሆን በርካታ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያዎች እያደረገ ይገኛል፡፡ የሀገሪቱን የንግድ ሥርዓት ለማዘመን የግሉ ዘርፍ ከመንግሥት ጋር በትብብር ሊሠራ ይገባል፡፡ እንደ አቶ ተመስገን ገለጻ፤ መንግሥት የንግድ ዘርፉን ፍትሐዊ፣ ተደራሽና ተወዳዳሪ እንዲሁም ሀገሪቱን የንግድና ኢንቨስትመንት መዳረሻ ለማድረግ እየሠራ ነው። በተለይም ለንግዱ ዘርፉ የፋይናንስ አቅራቢ የሆኑ የባንኮች ድርሻ በከፍተኛ ሁኔታ እንዲያድግ ተደርጓል፡፡ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ማሻሻያው ለግሉ ዘርፍ ጥያቄ መልስ የሚሆን ነው ብለዋል።

የንግድ ሥርዓታችን ካለበት ኋላ ቀር የአሠራር ሥርዓት ተላቆ ቀልጣፋና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ እንዲሆን በመንግሥት በኩል አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን በማዋቀር ስኬታማ ተግባራት እየተከናወኑ ነው ያሉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የሀገሪቱን የንግድ ሥርዓት ለማዘመን የግሉ ዘርፍ ከመንግሥት ጋር በትብብር እንዲሠራም ጥሪ አቅርበዋል።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ካሣሁን ጎፌ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ መንግሥት ተወዳዳሪ የንግድ ሥርዓትን ለመገንባት፣ የገቢና የወጪ ንግዱን ለማሳለጥ በርካታ የፖሊሲና የሕግ ማሻሻያዎችን አድርጓል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

መንግሥት ካደረጋቸው ማሻሻያዎች ውስጥ በቅርቡ የተደረገው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ይጠቀሳል ያሉት ካሣሁን ጎፌ (ዶ/ር)፤ መንግሥትና የግሉ ዘርፍ መናበብ፣ መቀናጀትና መወያየት ከቻሉ የምናስባትን ታላቅ ሀገር በአጭር ጊዜ እውን ማድረግ ይቻላል ብለዋል።

በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ ምክክር መደረጉ የንግድ ሥርዓቱን ለማዘመን፣ በዘርፉ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት፣ የልማት አጋርና አብሮ የመሥራት ባሕልን ለማዳበር ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያበረክታል ሲሉ ገልጸዋል።

መንግሥት ከግሉ ዘርፍ ጋር ተቀራርቦ የመሥራትን ባሕልን ለማሳደግ ቁርጠኛ ነው ሲሉ አስታውቀዋል። በመድረኩ የቡና ምርትን በከፍተኛ ደረጃ የተቀበሉ ሳዑዲዓረቢያ፣ አሜሪካና ጀርመን፤ የአበባ ምርትን እንግሊዝ፣ ኔዘርላንድ፣ ሳዑዲዓረቢያ መሆናቸው ተገልጿል። ሕንድ፣ ፓኪስታን፣ ኬንያ በጥራጥሬ ምርት፤ የተባበሩት ዓረብ ኤሜሬትስ፣ እሥራኤልና ቱርክ የቅባት እህሎችን በከፍተኛ ደረጃ በመግዛት እውቅና ተሰጥቷቸዋል።

በአጠቃላይ ለ11 የውጭ ሀገራት ቡና፣ አበባ፣ የቅባት እህልና የጥራጥሬ ምርቶችን በመግዛት የላቀ አፈጻጸም ላስመዘገቡ ሀገራት እውቅና ተሰጥቷል። እውቅናው የኢትዮጵያን ምርት ከገዙ ሀገራት በተጨማሪ ለክልሎች፣ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ለሚገኙ አስመጪና ላኪዎች፣ ለሰንበት ገበያዎችና ለሱፐርማርኬቶች ተሰጥቷል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ኢትዮጵያ ለቀጣናው ሠላም እና መረጋጋት ስጋት የሚሆኑ እንቅስቃሴዎችን በትኩረት ትከታተላለች

የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ካለው ስትራቴጂክ ጠቀሜታ አኳያ የብዙዎችን ትኩረት የሚስብ፣ ሰፊ ጣልቃ ገብነት የሚስተዋልበት፣ በዚህም ምክንያት ከስድስት አስርት ዓመታት በላይ ባለመረጋጋት እና በግጭት ውስጥ የቆየ አካባቢ ነው። የአካባቢው ሀገራት ሕዝቦችም የሚፈልጉትን ሠላም እና ልማት እውን ማድረግ ሳይችሉ ዓመታትን በብዙ ፈተናዎች ውስጥ ለማለፍ የተገደዱ ናቸው።

በተለይም በሶማሊያ የተፈጠረው መንግሥት አልባነት እንደ አልሸባብ እና አይ ኤስ ኤስ የመሳሰሉ ጽንፈኛ እና አሸባሪ ኃይሎች በአካባቢው በስፋት እንዲንቀሳቀሱ፣ ከአካባቢው አልፈው ለዓለም ስጋት እንዲሆኑ አድርጓል። ችግሩ በቀጣናው ዘላቂ ሠላም ለማምጣት የሚደረገውን አሕጉራዊ ሆነ ዓለም አቀፍ ጥረት ፈትኗል ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ እና መንግሥት ለሶማሊያ ሕዝብ ካለው ቅርበት /ወንድምነት/ የተነሳም ዓለም አቀፍ፣ አሕጉራዊ እና አካባቢያዊ የሠላም ማስከበር ተልዕኮዎችን ወስዶ ሕዝቡ ከጽንፈኛ እና ሽብርተኛ ቡድኖች የሚደርስበት ፈተና ለማቅለል፣ የተሻለ የሠላም አየር እንዲተነፍስ ለማስቻል ብዙ መስዋዕትነት የጠየቁ ወታደራዊ ተልዕኮዎችን ወስዶ በስኬት ተወጥቷል።

በዚህም የሶማሊያ ሕዝብ ከጽንፈኛ እና ከአክራሪ ቡድኖች የሚደርስበትን አስቸጋሪ ፈተናዎች ተሻግሮ አንጻራዊ የሆነ የሠላም አየር እንዲተነፍስ አድርጓል። ከዚህም ባለፈ ቡድኖቹ ከሶማሊያ ውጪ ባሉ የአካባቢው ሀገራት ሠላም እና መረጋጋት ላይ ጫና እንዳይፈጥሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ እና መንግሥት ያበረከቱት አስተዋፅዖም የማይተካ ነው ።

ይህ ብዙ የሕይወት መስዋዕትነት የጠየቀ የኢትዮጵያ አስተዋፅዖ አካባቢውን በማረጋጋት ሆነ በአካባቢው የተሻለ ሠላም ለማስፈን ስለነበረው ድርሻ ከማንም ይልቅ ለሶማሊያ ሕዝብ የተሰወረ አይደለም። የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ከሁለት አስርት ባላነሰ ጊዜ በሶማሊያ ያደረገው ቆይታም የዚሁ እውነታ ተጨባጭ ማሳያ ነው።

ይህንን ዓለም አቀፍ እውቅና ያተረፈ በሕይወት መስዋዕትነት ላይ የተመሠረተ የኢትዮጵያን የክፉ ቀን አጋርነት፣ ለማጠልሸት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሶማሊያ መንግሥት በኩል የሚስተዋሉ ያልተገቡ አካሄዶች ለሶማሌ ሕዝብ እና ለታሪክ የሚተዉ ናቸው። የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ የሞራል እና የታሪክ ተጠያቂነት ማስከተላቸው የማይቀር ነው።

የሶማሌ መንግሥት ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ያሉትን አንዳንድ ልዩነቶች በድርድር ከመፍታት ይልቅ፣ በአካባቢው ሠላም እና መረጋጋት መስፈኑ ብሔራዊ ጥቅማችንን ይጎዳዋል የሚሉ ኃይሎችን ጣልቃ በማስገባት፣ በአካባቢው ውጥረትን ለማንገሥ እየሄደበት ያለው፣ የተሳሳተ የዜሮ ብዜት መንገድ የሶማሊያ ሕዝብ ፍላጎት ነው ተብሎም አይታመንም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ እና መንግሥት የአካባቢው ሠላም ከሁሉም በላይ ለራሳቸው ሆነ ለአካባቢው ሀገራት የጋራ ተጠቃሚነት ስትራቴጂክ አቅም እንደሆነ ያምናሉ። በየትኛውም ሁኔታ በአካባቢው የሠላም ስጋት የሚፈጥር እንቅስቃሴ በአንድም ይሁን በሌላ ስለሚመለከታቸው ሁኔታውን አቅልለው የሚመለከቱት አይሆኑም።

በተለይም አካባቢውን ወደ አለመረጋጋት ሊወስዱ የሚችሉ የተለያዩ ፍላጎቶችን ያላቸው ኃይሎች ወደ አካባቢው የሚያደርጉትን የትኛውንም በዓይነት ያልተገባ እንቅስቃሴ በልዩ ትኩረት ይከታተላሉ። የነዚህ ኃይሎች ዋንኛ ተልዕኮ በአካባቢው አለመረጋጋት ለመፍጠር በመሆኑም ጉዳዩን በብሔራዊ ጥቅም እና ሠላም ላይ የሚደረግ ትንኮሳ አድርገው ይመለከቱታል ።

የአካባቢው ሀገራት ሕዝቦች ዕጣ ፈንታ የሚወሰነው በአካባቢው ሊኖር በሚችለው ሠላም እና መረጋጋት፣ ከዚህ በሚመነጭ ልማት እንደሆነ የኢትዮጵያ መንግሥት እና ሕዝብ በከፍተኛ ሁኔታ ያምናሉ። ለዚህም ሲሉ በሠላም ሆነ በልማት ዙሪያ ከአካባቢው ሀገራት ጋር ፍትሐዊ የጋራ ተጠቃሚነትን መሠረት ባደረገ መልኩ አብሮ መንቀሳቀስ የሚያስችሉ ስትራቴጂ ነድፈው እየተንቀሳቀሱ ነው።

ኢትዮጵያ ለሶማሊያ ሕዝብ ዘላቂ ሠላም ለማምጣት የከፈለችው የሕይወት መስዋዕትነትም ይህንኑ ታሳቢ ያደረገ፣ አሁን ላይ አካባቢውን በኢኮኖሚ ለማስተሳሰር የምታደርገውም ጥረት ከዚሁ የመነጨ ነው። በቀጣይም በአካባቢው ዘላቂ ሠላምን በማስፈን ብሔራዊ ጥቅሞቿን ለማስከበር የምትሄድበት ኃላፊነት የተሞላበት አካሄድ የዚሁ እውነታ ተጨባጭ ማሳያ ሊሆን የሚችል ነው ።

ከዚህ ውጪ በየትኛውም መንገድ ለሀገሪቱ ሆነ አጠቃላይ ለሆነው ለቀጣናው ሠላም እና መረጋጋት ስጋት ሊሆኑ የሚችሉ ጣልቃ ገብነቶችን፣ ለቀጣናው ሀገራት ሕዝቦች እውነተኛ ሠላም እና ልማት ስትል በትኩረት ትከታተላለች፣ አስፈላጊም ሆኖ ሲገኝ ሠላሟን እና ብሔራዊ ጥቅሞቿን ስጋት ውስጥ የሚጨምሩ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ኃላፊነት በሚሰማው መንገድ አስፈላጊውን እርምጃ ትወስዳለች።


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የኮሪደር ልማቱ ይዞት የመጣውን ትሩፋት ሙሉ ለማድረግ

ስሜነህ ደስታ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቁርጠኛ አካሄድ በመከተል የኢትዮጵያና የአፍሪካ መዲና የሆነችውን አዲስ አበባን በኮሪደር ልማቱ በመታገዝ አዲስ እንዲሁም አበባ እያደረገ ይገኛል። ይህ ተግባር ሲከናወን ከተማዋ አዲስ እና ውብ ከመሆኗ በተጨማሪ የተገኙ ሌሎች በጎ ትሩፋቶችም አሉ።

ከእነዚህ ትሩፋቶች አንዱ በኮሪደር ልማቱ የተተከሉ ተክሎች ለዓይን እይታ ማራኪ ከመሆናቸው በተጨማሪ ለአየር ንብረት መታደስ የሚያበረክቱት አስተዋፅዖ ከፍ ያለ ነው። ሣሩ፣ የተለያዩ የዛፍ ዝርያዎችን ጨምሮ ዘንባባዎቹ የከተማዋን አረንጓዴ ስፍራ በማሳደግ የሚያበረክቷቸው ሁለንተናዊ አስተዋፅዖ ለመገመት የሚከብድ አይሆንም ።

የኮሪደር ልማቱ ሌላው ትሩፋት የመኪና መንገዱ እንዲሁም የእግረኛው መተላለፊያ ሰፋ ብሎ ስለተሠራ ሹፌሮች በአስፋልት ላይ መኪናቸውን ዘና ብለው ማሽከርከር መቻላቸው ነው። እግረኞችም መኪናን እየተሻሹና ከመኪና ጋር እየተገፋፉ ከመንቀሳቀስ ተገላግለዋል። ይህም በመሆኑ መኪና በአስፋልቱ፣ እግረኛው በጎዳናው በመንቀሳቀሱ የመኪና አደጋ እየተስተዋለ አይደለም።

እኔ በብዛት በምንቀሳቀስበት የኮሪደር ልማቱ በተሠራባቸው በአራት ኪሎ - ፒያሳ መንገድ እና አራት ኪሎ - ቀበና - መገናኛ መንገድ ከዚህ በፊት የማየው የትራፊክ አደጋ አሁን ላይ እያስተዋልኩኝ አይደለም።

እንደውም ቀደም ሲል አብዛኛው እግረኛ ሕግ የማያከብር፣ በፈለገበት ቦታ የሚሻገር፣ እንዲሁም አስፋልት ላይ የሚንቀሳቀስ የነበረው አሁን ላይ በአብዛኛው በእግረኛ መንገድ የሚሄድ፣ የእግረኛ መሻገሪያ እየፈለገ የሚሻገር መሆኑን ለመታዘብ ችያለሁ። ይህም ከኮሪደር ልማቱ የተገኘ ሌላው ትሩፋት ነው። ይህ ትሩፋት በከተማዋ ለመኪና አደጋ መቀነስ የሚያበረክተው አስተዋፅዖ ከፍተኛ ይሆናል እላለሁ።

ቀደም ባለው ጊዜ ሕግ የማያከብረው አብዛኛው እግረኛ ብቻ ሳይሆን ባለመኪኖችም ነበሩ። ለአብነት ለመጥቀስ ያህል አራት ኪሎ ከትምህርት ሚኒስቴር አጠገብ ያለው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በር ላይ በእግረኛ መንገድ ላይ መኪኖች ተደርድረው ስለሚገኙ እግረኛው ወደ አስፋልቱ ወጣ ብሎ ለመጓዝ ይገደድ ነበር።

መኪኖቹ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በእግረኛ መንገድ ላይ የሚቆዩት ሁሌም ንግድ ባንኩ በሥራ ላይ እስካለ ድረስ መደበኛ የመኪና ማቆሚያ እስኪመስል ድረስ ሃይ ባይ ሳይኖራቸው ባለጉዳዮች እየተፈራረቁ ያቆሙበት ነበር። አሁን እግረኛ በእግረኛ መንገዱ፣ ባለመኪናው በአውራ መንገዱ ይነጉዳል።

ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት የኮሪደር ልማት በተሠራባቸው ሥፍራዎች አብዛኛው እግረኛ ሕግ እያከበረ ነው የሚሄደው። የመኪና መንገዱን እየተዳፈረ መሄድ አይደለም፣ የብስክሌት መሄጃውን እንኳን አብዛኛው እግረኛ እየተዳፈረ አይሄድም። ብስክሌት እየተንቀሳቀሰበት እንዳልሆነ እያወቀ ክፍት ነው ብሎ አብዛኛው እግረኛ አይሄድበትም፣ ተው አትሂድ የሚለው አሠራሩና ሕሊናው ነው። ሕሊናው የሚያዘው እግረኛ ማግኘት መቻሉ ታዲያ የኮሪደር ልማቱ ትሩፋት ነው አያስብልም ትላላችሁ? ።

**የብስክሌት መሄጃውን እንኳን አብዛኛው እግረኛ እየተዳፈረ አይሄድም፡፡ ብስክሌት እየተንቀሳቀሰበት እንዳልሆነ እያወቀ ክፍት ነው ብሎ አብዛኛው እግረኛ አይሄድበትም፤ ተው አትሂድ የሚለው አሠራሩና ሕሊናው ነው፡፡ ሕሊናው የሚያዘው እግረኛ ማግኘት መቻሉ ታዲያ የኮሪደር ልማቱ ትሩፋት ነው አያስብልም ትላላችሁ?**

ሌላው ትሩፋት ደግሞ በኮሪደር ልማቱ የእግረኛ መንገዶች ላይ የተሠሩት የእግረኛ ማረፊያ(መቀመጫ) አግዳሚዎች ናቸው። እነዚህ መቀመጫዎች እግረኛ በሚጓዝበት ወቅት ቢደክመው አረፍ ብሎ ከድካሙ እፎይታ ያገኝበታል፣ አንዳንዶቹ መቀመጫዎች ጥላ ሥር ስለሆኑ አረፍ በማለት ከፀሐይ በመጠለል ማሳለፍ የሚቻልባቸው ናቸው። አስፈላጊም ከሆነ ቁጭ ብሎ ለማሰላሰል መቀመጫዎቹ ምቹ ናቸው።

እዚህ ላይ ልጠቅስ የምፈልገው ጉዳይ መቀመጫዎቹ ከተጠቃሚዎቹ ቁጥር አንጻር መጠነኛ ስለሆኑ ተቋማት በበራቸው ላይ ሆነ አመቺ በሆኑ አቅራቢያቸው ላይ ሁለትም ሆነ ሦስት ማረፊያ የሚሆኑ መቀመጫዎች በማዘጋጀት ማኅበራዊ ኃላፊነታቸው ቢወጡ መልካም ነው እላለሁ።

የኮሪደር ልማቱ ሌላው ትሩፋት የምለው ደግሞ አራት ኪሎ ትምህርት ሚኒስቴር አጠገብ የተሠራው የውስጥ ለውስጥ የእግረኛ መንገድ ነው። ይህ የእግረኛ መንገድ የትራፊክ መጨናነቅንና አደጋ ከመቀነስ በተጨማሪ በውስጡ የተለያዩ አገልግሎቶች ማግኘት ማስቻሉ የሚጠቀስ ነው። የተሳፋሪ መጫኛና ማውረጃ ስፍራ መዘጋጀቱም ሌላው ተጠቃሽ ትሩፋት ነው።

በአሁኑ ሰዓት አምስቱም የኮሪደር ልማት ሥራዎች ከአንዳንድ ጥቃቅን የማጠናቀቂያ ሥራዎች በስተቀር በአብዛኛው ተሠርተው አገልግሎት እየሰጡ ነው። በቅርቡ ተጠናቆ ለተጠቃሚዎች ክፍት የተደረገው ከቦሌ ኤርፖርት ጀምሮ መገናኛ - ሲኤምሲ የሚደርሰው የመጀመሪያው ዙር አምስተኛው የኮሪደር ልማት የቀላል ባቡር የሐዲድ መሥመሩ ፈታኝ ቢሆንበትም በርካታ ነገሮችን አካቶ በማየቴ አድናቆቴን በዚህ አጋጣሚ እገልጻለሁ። ይህንን እንድንመለከት እና እንድንገለገልበት ላደረጉ ከላይ እስከ ታች ላሉ የልማቱ ተሳታፊዎች ሁሉ ምስጋና አቀርባለሁ።

አድናቆትና ምስጋና በማስከተል የምሰጠው ቢስተካከሉ የምለው፣ የፍሳሽ መቀበያ ቱቦዎች በአንዳንድ ስፍራዎች በሚገባው ልክ ባለመዘጋጀታቸው ዝናብ ሲዘንብ ፍሳሹ ጎርፍ ሆኖ እግረኞችንም ሆነ ተሽከርካሪዎችን እያስቸገረ ስለሆነ ለዚህ የሚሆን ማስተካከያ ቢደረግ መልካም ነው እላለሁ።

ከዚህ በተጨማሪ ለእግረኛ ተብሎ የተሠራው መንገድ አንዳንድ ቦታ ቴራዞው አዳላጭ በመሆኑ ዝናብ ሲዘንብ እያንሸራተተ ሰው ሲጥል አይቻለሁ፣ በተለይ ራስ መኮንን ድልድይ አካባቢ ኢትሆፍ እና ቲ- ሩም ሕንጻ ፊት ለፊት ያለው የተነጠፈው ቴራዞ እንዳያንሸራትት በሚል በኦክስጅን እየተሞቀ እንዲሻክር ማስተካከያ ሲደረግለት ለማስተዋልም ችያለሁ።

ይህ ከሚሆን ይልቅ በቅድሚያ የማያንሸራትቱ ቴራዞዎች ቢዘጋጁ ኖሮ ሰዎች ከመውደቅ ይድናሉ፣ ተጨማሪ ወጪ ወጥቶ ማስተካከያ ማድረግም አያስፈልግም ነበር። ይሄን የመሰሉ ሁኔታዎች ወደፊት በሚሠሩ የኮሪደር ልማቶች እንዳይከሰቱ ትምህርት መውሰድ ይገባል። በአንዳንድ አካባቢዎች የተሠሩት የመፀዳጃ ቤቶች ሙሉ ለሙሉ የተጠናቀቁ ቢሆንም አገልግሎት እየሰጡ አይደለምና በፍጥነት አገልግሎት እንዲሰጡ ቢደረግ መልካም ነው ።

ሌላው ቀደም ሲል ሲነሳ የነበረው እና በጠቅላይ ሚኒስትሩ በተደጋጋሚ የተነገሩት የልማት ሥራዎች ሲሠሩ፣ በልማት የሚነሱ ዜጎች ሳይጉላሉ መሠረተ ልማቱ የተሟላ ምትክ ቤትና ቦታ የማግኘታቸው ሁኔታ እና በማኅበራዊ ኑሯቸውም እንዳይራራቁ አንድ ስፍራ የሚያገኙበት ሁኔታ የመመቻቸት ጉዳይ ነው። ለዚህ ደግሞ የሚመለከታቸው አካላት በኃላፊነት መንፈስ ሊንቀሳቀሱ ይገባል።



ወ/ሪት ሐና ተልህኩ

# የካፒታል ገበያ ‘ሳንድቦክስ’ ከቁጥጥር ሥራው በተጨማሪ ፈጠራን ያበረታታል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- የካፒታል ገበያ ቁጥጥር ሳንድቦክስ ከቁጥጥር በተጨማሪ ፈጠራን በማጎልበት አዳዲስ ምርቶችና አገልግሎት እንዲስፋፉ የሚያግዝ መሆኑን የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣን አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ የፈጠራ ባለቤቶች፣ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች፣ ፊንቴኮችና አዳዲስ ኩባንያዎች ደኅንነቱ በጠበቀ ሁኔታ አዳዲስ ምርቶችና አገልግሎቶቻቸውን እንዲያስተዋውቁ የሚያስችል የቁጥጥር ሳንድቦክስ (regulatory sandbox) ትናንት በይፋ አስጀምሯል።

የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ወይዘሪት ሐና ተልህኩ በዕለቱ እንዳስታወቁት፤ ከቁጥጥር በተጨማሪ ፈጠራን በማጎልበት አዳዲስ ምርቶችና አገልግሎት እንዲስፋፉ የሚያግዝ ነው፡፡

የቁጥጥር ሳንድቦክስ ሲዘጋጅ የተለያዩ ሀገራት ልምዶች ተካተውበታል ያሉ ሲሆን ዋና ዓላማውም ፈጠራን ማበረታታት፣ የቁጥጥር ልምምድ ማጎልበት ነው። እንዲሁም የባለሥልጣኑ ዋና ኃላፊነት የገበያውን ትስስር መጠበቅ በመሆኑ አዳዲስ ፈጠራዎች ሲተዋወቁ የሚጎዳ ገበያ እንዳይኖር ማድረግ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

የቁጥጥር ሳንድቦክስ የፈጠራ ሥራዎች፣ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች፣ ፊንቴኮችና አዳዲስ ኩባንያዎች ደኅንነታቸው በተጠበቀ መልኩ የካፒታል ገበያውን ሁኔታ መቆጣጠር እንዲሁም የፈጠራ ባለቤትነት የሚያስጠብቅ ነው ያሉት ወይዘሪት ሐና፣ በተጨማሪም በአዲስ ካፒታል ገበያ ምርትና አገልግሎት ማስፋት የሚያስችል ነው ብለዋል፡፡

ወይዘሪት ሐና አክለውም፤ የቁጥጥር ሳንድቦክስ ለተቆጣጣሪዎችም ሆነ ለፈጠራ ባለቤቶች ለአዲስ ፋይናንሻል ምርቶችና አገልግሎቶች ደኅንነት እንዲሁም ውጤታማነት በማረጋገጥ የጋራ ተጠቃሚ የሚያሳድግ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

የካፒታል ገበያ ቁጥጥር ሳንድቦክስ አዳዲስ ምርቶችና አገልግሎት እንዲስፋፉ ምቹ ሁኔታዎች በመፍጠር የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለማሳደግ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለውም ነው ወይዘሪት ሐና የገለጹት፡፡

እንደ ሐና ገለጻ፤ ኢኒሼቲቩ በኢትዮጵያ ግልጽ፣ ተዓማኒና አካታች የኢኮኖሚ እድገት ለማስመዝገብ ያግዛል። የቁጥጥር ሳንድቦክስ በኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ካፒታል ገበያ ለመገንባት እንዲሁም መጠነ ሰፊ የሆነ የካፒታል ገበያ እድገት ለማረጋገጥ የሚያግዝ ነው፡፡

በተጨማሪም የሀገር ውስጥ እና የውጭ ኢንቨስትመንት ለመሳብ፣ የሥራ ዕድል ፈጠራ እንዲሁም በፋይናንስ ተቋማት መካከል የገበያ ውድድር መፍጠር የሚያስችል መሆኑን ጠቁመዋል።

የቁጥጥር ሳንድቦክስ የካፒታል ገበያ በኢትዮጵያ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ነው ያሉት ወይዘሪት ሐና፤ በቀጣይም ደኅንነቱ የተጠበቀ የፋይናንሻል ገበያ ሥርዓት ዝርጋታ የሚከናወንበት ጭምር እንደሆነ ተናግረዋል።

የቁጥጥር ሳንድቦክስ በየዘርፉ የሚኖሩ አዳዲስ ጉዳዮችንና ሥራ ፈጣሪዎችን ለማበረታታት፣ የቁጥጥር ሥራውና ፈጠራን በአንድ ላይ ለማጣጣም ታስቦ የተዘጋጀ መሆኑን ጠቅሰው፤ ለቁጥጥር የተዘጋጁ የተለያዩ የሕግ ማዕቀፎች ለፈጠራ እንዲመች አድርጎ ለማቅረብ የሚያስችል ነው ብለዋል፡፡

በተጨማሪም፤ ከካፒታል ገበያው ጋር የተገናኘ ፈጠራ ነክ አገልግሎቶችና ምርቶች ለማቅረብ ለሚፈልጉ አካላት የሚያገለግል እንደሆነም አስረድተዋል፡፡

# የሶማሊያ አካሄድና ቀጣዩ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

መስዋዕትነት የሚያጠለሹ ተከታታይ መግለጫዎች ሲወጡ ኢትዮጵያ በዝምታ እንድታልፍ ከአንዳንድ ወገኖች በኩል ፍላጐት መኖሩ እንደሚታይ መግለጫው ጠቅሶ፤ ሌሎች ተዋናዮች የአፍሪካ ቀንድ ክልልን ለማተራመስ እርምጃ ሲወስዱ ኢትዮጵያ በዝምታ አትመለከትም፡፡ ይህም በመሆኑ በቀጣናው የብሔራዊ ደኅንነቷን አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉ ሁኔታዎችን ሁሉ በንቃት እየተከታተለች ትገኛለች ሲል መግለጫው ያብራራል፡፡

ኢትዮጵያ ለሶማሊያና ለአካባቢው ሠላምና ፀጥታ መስፈን፣ ለጋራ ዕድገት እና በክልሉ ያሉ ሕዝቦች መካከል ያለውን የጠበቀ የርስ በርስ ትስስር ይበልጥ እንዲጎለብት ያላሰለሰ ጥረት ስታደርግ ቆይታለች፡፡

ኢትዮጵያ ከሶማሊያ መንግሥት ጋር ያለውን ወቅታዊ አለመግባባት ለመፍታት እንዲያስችል በተዘጋጁ የውይይት መድረኮች ላይም በንቃት ተሳትፎ አድርጋለች የሚለው መግለጫው በእነዚህ ንግግሮች ተጨባጭ ውጤቶችም ታይተዋል። የሶማሊያ መንግሥት እነዚህን ሠላም ለማስፈን የሚደረጉ ጥረቶች ከማጠናከር ይልቅ ቀጣናውን ለማተራመስ ከሚሹ የውጭ ኃይሎች ጋር እየሠራ ይገኛል፡፡

በሶማሊያ ለማሰማራት የታቀደውን አዲስ የሠላም ተልዕኮ የማዘጋጀት እና የመፍቀድ ኃላፊነት ያለባቸው አካላት ሁሉ በቀጣናው የሚገኙና ቀደም ሲል ወታደር አዋጭ የሆኑ ሃገራትን ተገቢ የሆኑ ስጋቶች ሁሉ ትኩረት ሊሰጡ ይገባል፡፡ ለአጭር ጊዜ ፍላጎታቸው እና ከንቱ ዓላማቸው ሲሉ በክልሉ ውጥረትን ለማቀጣጠል የሚሞክሩ ኃይሎች ዕኩይ ተግባራቸው የሚያስከትሏቸውን መዘዞች መሸከም ይኖርባቸዋል፡፡

ቀደም ሲል አሕጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ አሸባሪ ቡድኖች ላይ የተገኘውን አበረታች ውጤት አደጋ ላይ የሚጥሉና የሚቀለብሱ ድርጊቶች ኢትዮጵያ አትታገስም ሲልም መግለጫው ያስጠነቅቃል።

ኢትዮጵያ የባሕር በር የምታገኝበትን የመግባቢያ ሰነድ ታኅሣሥ 22 ቀን 2016 ዓ.ም. አዲስ አበባ ላይ ከሶማሊላንድ ጋር መፈራረሟ ይታወሳል፡፡ ስምምነቱን ተከትሎ ኢትዮጵያና ሶማሊያ ዲፕሎማሲያዊ ውጥረት ውስጥ ገብተዋል፡፡ ሶማሊያ በቀጥታ ከኢትዮጵያ ጋር ከማውራት ይልቅ ከኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ጋር በጉዳዩ መምከርና መፍትሔ ባይሆንም ማስፈራራትን መርጣለች፡፡

የሶማሊያ ባለሥልጣናት አልሻባብን እየተዋጋ ከ15 ዓመታት በላይ የቆየው የኢትዮጵያ ሠራዊት እንዲወጣ በተደጋጋሚ መጠየቃቸው ይታወሳል፡፡ የሶማሊያና የኢትዮጵያ ግንኙነት መሻከሩን ተከትሎ ሀገሪቷ ወርቅ ላበደረ ጠጠር እንዲሉ ቀጣናውን ለማተራመስ ከሚሹ የውጭ ኃይሎች ጋር እየሠራች ነው፡፡

ሶማሊያ ከውጭ ኃይሎች ጋር እየሠራች መሆኗ ለኢትዮጵያ ምን ስጋት አለው? ቀጣይ የኢትዮጵያ የቤት ሥራ ምን መምሰል አለበት? በሚሉ ጉዳዮች ዙሪያ የዘርፉ ምሑራን ሀሳባቸው አካፍለውናል፡፡

በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት የአፍሪካ ቀንድ ተመራማሪ ረዳት ፕሮፌሰር በፍቃዱ ቦጋለ እንደሚገልጹት፤ ሶማሊያ የኢትዮጵያ ባላንጣ ከሆኑ የውጭ ኃይሎች ጋር የጀመረችው የተለየ ግንኙነት ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡ እነዚህ የውጭ ኃይሎች ለኢትዮጵያ ሠላም አስበው ስለማያውቁ ጥንቃቄና ትኩረት ይፈልጋል፡፡

ከጥንት ዘመን ጀምሮ በተለያየ አግባብ ኢትዮጵያን ያዳከማል የሚሉትን አካሄድ ሲከተሉ የቆዩ መሆናቸውንም ረዳት ፕሮፌሰር በፍቃዱ ገልጸዋል፡፡

በሶማሊያ ጋባዥነት ወደ ቀጣናው እየገቡ ያሉ እነዚህ የውጭ ኃይሎች የኢትዮጵያን የባሕር በር ጥያቄን ለማዳፈን እየሠሩ ነው ሲሉም ያስረዳሉ፡፡

በአንጻሩ ሶማሊያ ለበርካታ ዓመታት ችግር ሲገጥማት ከችግሯ ለማላቀቅ እነዚህ ኃይሎች ምንም አይነት ድጋፍ ሲያደርጉ አልታዩም ያሉት ምሑሩ፤ ኢትዮጵያ ከፍተኛ መስዋዕትነት በመክፈል ሶማሊያ እንድትረጋጋ አድርጋለች ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

እስካሁን ድረስ የሶማሊያ ችግር ያልታያቸው ኃይሎች ዛሬ ለምን ጉዳዩ እንደሳባቸው ትኩረት ሰጥቶ ክትትል ማድረግ ይገባል፡፡ የገዘፈ ባይሆንም ስጋት ስላለው ጥንቃቄና ትኩረት ይሻል ሲሉም ያስገነዝባሉ፡፡

ኢትዮጵያ በቀጣይ በምትሠራቸው የዲፕሎማሲ፣ የፀጥታ፣ ኢኮኖሚና ወታደራዊ ሥራዎቿ አዲሱን የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች አካሄድ ትኩረት ውስጥ ያስገቡ እንዲሆኑ ያስገድዳልም ብለዋል፡፡

በተለይ የተለያዩ የሶማሊያ ልሂቃንን በመጠቀም ወደሚፈልጉት አጀንዳ የማምጣት እንቅስቃሴ መኖሩን ጠቅሰው፤ አሁን ደግሞ የኢትዮጵያንና የሶማሊላንድን የባሕር በር ስምምነትን ተከትሎ እነዚህ ኃይሎች ከማንኛውም ሀገር ቀድመው የሶማሊያን ሉዓላዊነት ለመጠበቅ ዝግጁ መሆናቸውን እየገለጹ ነው ይላሉ፡፡

እነዚህ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ባላንጣዎች ከአልሸባብ ጋር ተስማምቶ መሥራት አይችሉም የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰሩ፤ ምክንያቱም ሁለቱ የማይታረቁ ሀሳብ ያላቸውና አብረው ሊሠሩ የማይችሉ አካላት ናቸው ባይ ናቸው፡፡

ሶማሊያን ለማረጋጋት የሶማሊያ ፌዴራል መንግሥት ተቋማት በተለይ ወታደራዊ፣ ፖሊስና በየአካባቢው ያሉ የአስተዳደር መዋቅሮች እንዲጠናከሩ እነዚህ የውጭ ኃይሎች አንዳችም ፍላጎት የላቸውም ሲሉ ያብራራሉ፡፡

ሞቃዲሾ ላይ ቁጭ ብሎ የእነዚህ ኃይሎችን አጀንዳ የሚያስፈጽም አካል እስካለ ድረስ ቤተመንግሥቱን ሊጠብቁ ይችላሉ፡፡ ከዚያ በሻገር እንደ ኢትዮጵያ መስዋዕትነት ከፍሎ በሰፊው የሶማሊያ አካባቢ ሠላም እንዲመጣና አስፈላጊ ሲሆን አሸባሪዎችን የሚዋጋ አካል አይኖርም፡፡

የኢትዮጵያ ሠራዊት የአካባቢ አስተዳደሮችን መደገፍና ሕዝቡ ሲቸገር የራሱን ምግብ አካፍሎ የኖረ ነው፤ ይህን የሚያደርግ ሌላ አካል እንደማይኖር በመግለጽ፤ ሶማሊያ አካሄዷን መፈተሽ እንዳለባት ጠቁመዋል፡፡

እንደ ረዳት ፕሮፌሰር በፍቃዱ ማብራሪያ፤ ኢትዮጵያ የሶማሊያ ጎረቤት በመሆኗ በሶማሊያ የሚነድ እሳት በቀጥታ ወላፈኑ ኢትዮጵያን ይጎዳል፡፡ ከዚህ ቀደም ኢትዮጵያ ጉዳት ደርሶባታል፡፡ ኃላፊነትም ስለሚሰማት ለሶማሊያ መረጋጋት አስፈላጊውን ዋጋ እየከፈለች ነው፡፡ አሁን የሶማሊያ ሉዓላዊነት ያሳስበናል የሚሉት ኃይሎች በኢትዮጵያ ልክ ተንቀሳቅሰው የሶማሊያን ሠላምና ደኅንነት የማስከበር ፍላጎትም ሆነ ተነሳሽነት የላቸውም፡፡ ድንበር ተጋሪም አይደሉም፤ የጋራ ታሪክ የላቸውም፤ ኢትዮጵያ ከሶማሊያ ጋር ከታሪካዊ ግንኙነት ባሻገር የሶማሊያ ችግር በቀጥታ ስለሚጎዳት ለሠላም መስፈን ብዙ ዋጋ ከፍላለች ነው ያሉት፡፡

እነኝህ ኃይሎች በኢትዮጵያ ልክ በኃላፊነት የፖለቲካና የፀጥታ ሥራ ሊሠሩ አይችሉም ያሉት ተመራማሪው፤ ሶማሊያ ጉዳዩን በአፅንዖት ማየት አለባት፡፡ ችግሩ ሞቃዲሾ ላይ ያለው የሶማሊያ መንግሥት ይህን መረዳት አይፈልግም፡፡ በጊዜያዊ ስሜት በመነሳሳት ከፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎች ጋር መነጋገር መግለጫ መስጠትና መሰል እርምጃዎችን ከመውሰድ ባሻገር ስለ ሶማሊያ ዘላቂ ጥቅምና ሠላም እያሰበ አይደለም ብለዋል፡፡

አንዳንድ የአካባቢ አስተዳደሮች የእነዚህ የውጭ ኃይሎች አጀንዳ ሶማሊያን መርዳት፣ እንድትረጋጋ ማድረግ ሳይሆን ነገር ፍለጋ መሆኑን ያውቃሉ፡፡ ይህ ደግሞ የሚጎዳው የሶማሊያን ሕዝብ መሆኑን ስለሚገነዘቡ የኢትዮጵያ ወታደር ከሶማሊያ መውጣት የለበትም፤ እነዚህ ኃይሎች እንዲመጡብን አንፈልግም የሚሉ ድምፆችን እያሰሙ እንደሚገኙ ገልጸዋል፡፡

# በሀገራዊ ምክክሩ የሃይማኖት...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ሼክ ዑመር፤ የምክክሩ ስኬታማ መሆን እንደ ሃይማኖት አባት የሚያሳስበን በመሆኑ ከምንም ነገር በላይ ቅድሚያ በመስጠት የሚጠበቅብንን ኃላፊነት ለመወጣት እንሠራለን ይላሉ።

በየጫካው ያሉ ታጣቂዎች ርስ በርስ መገዳደልን እና ጦርነትን አቁመው ወደ ምክክሩ መምጣት አለባቸው የሚሉት ሼክ ዑመር፤ ሠላም የሚመጣው በምክክር እና በእርቅ በመሆኑ ታጣቂዎች በምክክሩ እንዲሳተፉ እንደ ሃይማኖት አባት ጥሪዬን አስተላልፋለሁ ብለዋል።

ሌላኛው የሲዳማ ክልል የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ምክትል ሰብሳቢ እና የፕሮቴስታንት ሃይማኖት አባት ቀሲስ እያሱ ተጊኞ እንደሚሉት ሀገራዊ ምክክሩ ሀገራዊ አንድነት ለማምጣት ወሳኝ ነው።

አሁን በኢትዮጵያ ያለውን ግጭት ለማስቀረት መመካከር አስፈላጊ መሆኑን ገልጸው፤ ምክክሩ በስኬት ከተጠናቀቀ ልዩነቶች በከፍተኛ ሁኔታ በማጥበብ ሠላምን እንደሚያመጣ ይገልጻሉ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አማኝ መሆኑን የሚናገሩት ቀሲስ እያሱ፤ የእምነት አባቶች በሚገባ ብናስተምር አሁን የተፈጠረው ችግር አይፈጠርም ነበር ይላሉ። ሁሉም የሃይማኖት አባቶች ወጣቶችን መምከር እና አንድነትን እና ፍቅርን ማስተማር ከቻሉ ትውልዱን ማዳን እንደሚቻል ተናግረው እንደ ሃይማኖት አባት የምንችለውን ሁሉ እናደርጋለን ይላሉ።

ጦርነት ደም ማፍሰስን፣ መፈናቀልን እና ጥላቻን የሚያመጣ በመሆኑ ሁሉም በተለይም መሣሪያ ይዘው እየተዋጉ ያሉ ወገኖች ግጭቶች በውይይት እንዲፈቱ ወደ ምክክሩ እንዲመጡም ጥሪ ያስተላልፋሉ።

የሃይማኖት አባቶችም ለምክክሩ ስኬታማ መሆን ወጣቱን ከመምከር ጀምሮ ኅብረተሰቡ በንቃት እንዲሳተፍ ምክር በመስጠት የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡም ይመክራሉ።

ሀገራዊ ምክክሩ እንደ ሀገር ከገባንበት የግጭት ቀውስ ለመውጣት በታሪክ አጋጣሚ የተገኘ ትልቅ ዕድል ነው። ምክክሩ ስኬታማ ሆኖ ሠላም ለማግኘት ብዙዎች በተስፋ እየተጠባበቁ በመሆኑ ስኬታማነቱ እንዲረጋገጥ በተለይ በማኅበረሰቡ ዘንድ ትልቅ ተቀባይነት ያላቸው የሃይማኖት አባቶች ለስኬቱ የላቀ ሚና መጫወት ይጠበቅባቸዋል።

# ቢሮው ለመጪው በዓል የግብርና...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

እንዲገቡ በትኩረት እየሠራ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ አስታወቀ፡፡ ከሁለት ሚሊዮን ሊትር በላይ የምግብ ዘይት ለማቅረብ መታቀዱም ተገልጿል፡፡

የቢሮው የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር አቶ ሰውነት አየለ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከአዲስ ዓመት ክብረ በዓል ጋር ተያይዞ በመዲናዋ ምርቶች ላይ የዋጋ ንረት እንዳይከሰትና የምርት እጥረት እንዳያጋጥም ቢሮው በትኩረት እየሠራ ይገኛል፡፡

እንደ አቶ ሰውነት ገለጻ፤ ቢሮው ለበዓሉ የሚውል ሁለት ሚሊዮን ሊትር የምግብ ዘይት፣ 36 ሺህ ኩንታል ስኳር፣ 36 ሺህ ኩንታል ጤፍ፣ ቀይ ሽንኩርት 100 ሺህ ኩንታል፣ ቲማቲም 30 ሺህ ኩንታል፣ 3 ነጥብ 5 ሚሊዮን እንቁላል፣ 10 ሺህ ኩንታል ስንዴ ዱቄትና መሰል ምርቶች ለማቅረብ አቅዷል፡፡

ቢሮው በበዓላት ወቅት የቁም እንስሳትንና የእንስሳት ተዋፅዖዎች ተፈላጊነት ስለሚጨምር አቅርቦቱን በማሳደግ ከፋብሪካዎች፣ ከአምራች ኢንዱስትሪዎችና ከክልል አምራቾች ጋር በቅንጅት እየተሠራ እንደሚገኝ አመላክተዋል፡፡

የበዓል ወቅትን መሠረት ያደረገ የምርት አቅርቦትን ለማሳደግ፤ ወደ መዲናዋ ምርት በስፋት እንዲገባና ኅብረተሰቡ በአማራጭ የግብይት ማዕከላት ምርት እንዲያገኝ የሚሠራና ሊፈጠሩ የሚችሉ ሕገ-ወጥ እንቅስቃሴዎችን የሚቆጣጠር ግብረ ኃይል በከተማዋ ደረጃ መቋቋሙን አቶ ሰውነት አስታውቀዋል።

በከተማው በሚገኙ የአቃቂ ቃሊቲ፣ የለሚ ኩራና የኮልፌ የግብርና ምርቶች የገበያ ማዕከላት ከነሐሴ 27 ቀን እስከ ጳጉሜን አምስት ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ የሚቆዩ የምርት ዓውደ ርዕዮችና ባዛሮች እንደሚዘጋጁ ጠቅሰው፤ ይህም ሸማቹን ማኅበረሰብ ከአምራቹ ጋር በቀጥታ ለመገናኘት ያግዛል ብለዋል።

ከዚህ በተጨማሪ በመዲናዋ መደበኛ የገበያ ሥፍራዎች የበዓል ግብይቱን ለማከናወን የሚያስችል የምርት አቅርቦት እየገባ መሆኑን አውስተው፤ ከ193 በላይ በሆኑ የእሁድ ገበያዎችን ላይ በመደበኛ ቀናት ጭምር ግብይት ለመፈጸም የሚያስችል ዝግጅት ተደርጓል ሲሉ አስረድተዋል።

ለበዓል ገበያ የአቅርቦት እጥረት እንዳይፈጠር የግብርና፣ የኢንዱስትሪ እንዲሁም የእርድ እንስሳትን ጭምር በብዛት ወደ አዲስ አበባ እንዲገቡ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

ኅብረተሰቡ በበኩሉ ደረሰኝን መሠረት ያደረገ ግብይት በመፈጸም ሕገ-ወጦችን ለመከላከል በሚደረገው ጥረት ተባባሪ ሊሆን ይገባል ያሉት አቶ ሰውነት ፤ በግብይት ሥርዓቱ ችግር ሲያጋጥም ሕገ-ወጥ ድርጊቶችን በማጋለጥና ለሚመለከታቸው አካላት ጥቆማ መስጠት እንደሚገባ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

# ወጣቶችና ፈጠራ

ክብረአብ በላቸው

በኢትዮጵያ በዓመቱ እስከ ሁለት ሚልዮን የሚጠጉ ወጣቶች ወደ ሥራው ዓለም ይቀላቀላሉ ወይም ሥራ ፈላጊ ይሆናሉ። ለዚህ ከፍተኛ ቁጥር ላለው ዜጋ በመንግሥት ወይም በግል ተቋማት እና ድርጅቶች የሥራ ዕድል መፍጠር ባለመቻሉ አብዛኛው ቁጥር ያለው ወጣት ለስራ አጥነት ይዳረጋል። ይህንን ችግር ለመፍታት ደግሞ ሥራ ጠባቂ ከመሆን ይልቅ ሥራ ፈጣሪ ሆኖ መገኘት ይገባል።

ሆኖም በኢትዮጵያ በርካታ ወጣቶች የስራ ፈጠራ ባለሙያዎች ቢሆኑም የፈጠራ ሀሳባቸውን ወደ ተግባር ለማዋል የመስሪያ ቦታ እጥረት፣ የብድር አቅርቦት አለመመቻቸት፣ የገበያ ትስስር አለመኖር እና የክህሎት ክፍተቶችና መሰል ችግሮች እንቅፋት ሆኖ ሲገጥማቸው ይስተዋላል።

አንድ ሰው የተሳካለት ሥራ ፈጣሪ ወይም ኧንተርፐረነር ለመሆን አዲስ የፈጠራ ሃሳብ ወሳኝ ነው። ከዚያ ሲቀጥል ደግሞ ሃሳቡን ተግባራዊ ማድረጊያ ገንዘብ ወሳኝ መሆናቸው አይጠረጠርም። ሆኖም፣ እነዚህ ሁለቱ ብቻ ሥራ ፈጣሪው የተሳካለት የቢዝነስ ሰው እንዲሆን አያስችሉትም። ሥራ ፈጣሪው፣ ስኬትን መቀዳጀት እንዲችል ወይም ጉዞው ወደ ስኬት የሚገሰግስ እንዲሆን፣ ዓይነተኛ የሆኑ የስብዕና መገለጫዎች ያስፈልጉታል። ታታሪነት፤ አርቆ አሳቢነትና ተስፋ አለመቁረጥ የመሳሰሉት የስብእና ባለቤት ሊሆን ይገባል። እንደ ሥራ ፈጣሪ፣ እነዚህ የስብዕና መገለጫዎች ወይም ጠባዮች ካሉት ሊያዳብራቸው፣ ከሌሉት ደግሞ እንደ አዲስ በውስጡ ኮትኩቶ ሊያሳድጋቸው ይገባል።

በቅርቡ የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ወጣቶች በዲጅታል ቴክኖሎጂ ላይ ያላቸውን ተሳትፎ ለማሳደግና ለማጠናከር በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ24ኛ ጊዜ “From Clicks to Progress: Youth Digital Pathways for Sustainable Development” (በሚል መሪ ቃል በኢትዮጵያ ደግሞ ለ21 ጊዜ “ወጣቶችን በቴክኖሎጂ ማብቃት ለዘላቂ ልማት ግቦች ስኬት” በሚል መሪ ቃል ዓለም አቀፍ የወጣቶች ቀንን አክብሯል።

በበዓሉም በአገር አቀፍ ደረጃ በወጣቶች አማካኝነት የተፈጠሩ የዲጂታል ውጤቶች የሆኑ የፈጠራ ሥራዎችን የያዘ ኤግዚብሽን ቀርቧል።

ወጣት ኦብሳ ሃምዛ በዚህ አውደ ርእይ ሥራዎቻቸውን ይዘው ከቀረቡ ወጣቶች መካከል አንዱ ነው። (አምራች ዶትኮም) የሚል መጠሪያ የተሰጠው የቴክኖሎጂ ኩባንያ መሥራች የሆነው ወጣቱ የቴክኖሎጂ ድርጅቱ በዋናነት ምን አይነት ሥራዎችን እንደሚሰራ ስናገር፤ የግብርና ምርቶችን ከአምራቾች ተቀብሎ በችርቻሮ ንግድ ላይ ለተሰማሩ ግለሰቦች እንደሚያቀርብ ይናገራል።


አንድ ምርት ተመርቶ ከፋብሪካ ወጥቶ ተጠቃሚው ጋር እስኪደርስ ድረስ በመሃል ከሰባት እስከ አስር ሰው እየገባ የራሱን ትርፍ ለማግኘት ጥረት ያደርጋል የሚለው ወጣት ኦብሳ፤ ይህ ጉዳቱ ለአብነት አንድ ምርት በአንድ መቶ ብር ከተገዛ በኋላ አንድ መንደር ላይ ወዳለ ሱቅ ሲደርስ 180 ብር ይሆናል። ባለሱቁ ደግሞ ሁለት መቶ ብር አድርጎ ለመጨረሻ ተጠቃሚው ይሸጣል። ይህ ጤናማ አካሄድ አይደለም ይላል።

‹‹ለዚህ ችግር መፍትሄ የሚሆን ቴክኖሎጂ ነው ይዘን የመጣነው›› የሚለው ኦብሳ፤ ዲጂታል የገበያ ማዕከል በመዘጋጀት አምራችና ገዥ በቴክኖሎጂው እንዲመዘገብና ገዥ የሚፈልገውን የምርት አይነትና ፍላጎት እንዲገልጽ በማድረግ ሶስተኛ ወገን ሳይኖር ለአብነት በፊት 200 ብር ይገዛ የነበረውን እቃ በ100 ብር እንዲያገኝ የሚያስችል አሰራር መሆኑን ይናገራል። ይህ ደግሞ ለኅብረተሰቡ እፎይታን የሚሰጥ መሆኑን ይገልጻል።

በኢትዮጵያ የኑሮ ውድነት መባባስ አንዱ ምክንያት ምርት ከማሳ እስከ ገበታ ባለው ሂደት ተሳታፊ የሆኑ አካላት የራሳቸውን ጥቅም ለማግኘት በሚያደርጉት ጥረት በሚፈጠር የንግድ ሰንሰለት መርዘም ምክንያት ነው የሚለው ወጣት ኦብሳ፤ ይህ ቴክኖሎጂ ግን አላስፈላጊ የደላሎች ጣልቃ ገብነትን በማስወገድ ለኑሮ መረጋጋቱ የራሱም አወንታዊ ሚና እንደሚጫወት ይናገራል።

የቴክኖሎጂ ፋይዳው ለአምራቾችም ትልቅ ነው የሚለው ወጣት ኦብሳ፤ ማንኛውም አምራች የሰውን ፍላጎት ባገናዘበ መልኩ ምርት ማምራት ከቻለ ምርቱ ሳይበላሽ ተጠቃሚው ጋር እንዲደርስ ይረዳዋል። በተጨማሪም ተደራሽነቱን በማስፋት ተጨማሪ የገበያ ትስስር መፍጠር እንዲቻል መንገድ እንደሚሆን ይገልጻል።

ይህንን ቴክኖሎጂ ለመፍጠር መነሻ ምክንያት



ወጣት ኦብሳ ሃምዛ

**ምርት በሚደበቅበት፣ አላግባብ ዋጋ ጭማሪ በሚደርግበት፣ አለመተማመን በበዛበትና የሰለጠነ አካሄድ በሌላው የኢትዮጵያ የገበያ ስርዓት በዚህ ቴክኖሎጂ አማካኝነት ችግሩን በማቃለል ሰዎች የሚፈልጉትን ምርት ከተለያዩ አምራቾች በቀላሉ ማግኘት እንዲችሉ እያደረጉ እንዳለ ይናገራል**



ወጣት አበበ ነጋሽ

ስለሆነው ነገር ወጣት ኦብሳ ሲናገር፤ `‹‹በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ወቅት ለመግዛት የምንፈልጋቸው እቃዎች ነበሩ። ነገር ግን የተለያዩ ቦታዎች ብንፈልግም ማግኘት አልቻልንም። እቃው አለ የተባለበት ስንሄድም በትክክል ጥረቱን የጠበቀ ምርት አልነበረም። ስለዚህ ለምን ይህንን ችግር ለመፍታት ሰዎች ባሉበት ቦታ ሆነው የሚፈልጉትንና ጥረቱን የጠበቀ አገልግሎት ማግኘት አይችሉም በሚል መነሻ ይህንን ቴክኖሎጂ ለመሥራት ተነስተናል ›› ሲል ሀሳቡ የመነጨበትን መንገድ ያብራራል።

ምርት በሚደበቅበት፣ አላግባብ ዋጋ ጭማሪ በሚደርግበት፣ አለመተማመን በበዛበትና የሰለጠነ አካሄድ በሌላው የኢትዮጵያ የገበያ ስርዓት በዚህ ቴክኖሎጂ አማካኝነት ችግሩን በማቃለል ሰዎች የሚፈልጉትን ምርት ከተለያዩ አምራቾች በቀላሉ ማግኘት እንዲችሉ እያደረጉ እንዳለ ይናገራል።

ማንኛውም ሰው (Kamrach.com) በተሰኘ ድህረገጽ አማካኝነት የአማርኛ፣ ኦሮሚኛ፣ ትግረኛና ሶማልኛ ቋንቋ በመጠቀም በቀላሉ አገልግሎቱን ማግኘት እንደሚችል የሚናገረው ወጣት ኦብሳ፤ የክፍያ ስርዓቱም ቀላልና ማንኛውም ሰው ሊረዳው በሚችለው መልኩ የተዘጋጀ ስለመሆኑ ይናገራል።

‹‹በአሁኑ ወቅት ከአንድ መቶ ሺህ በላይ አገልገሎት ፈላጊዎች ድረገጻችንን ጎብኝተዋል›› የሚለው ወጣት ኦብሳ፤ የአገልግሎት ፈላጊው ቁጥሩ ከግዜ ወደ ግዜ እየጨመረ መምጣቱ በርካቶች በቴክኖሎጂው የመጠቀም ፍላጐት እንዳለቸው የሚያሳይ እንደሆነ ይገልጻል።

መንግሥት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለይ ለቴክኖሎጂና ፈጠራ የሰጠው ትኩረት ይበል የሚያሰኝ ነው የሚለው ኦብሳ፤ ይህ የዓለም ወጣቶች ቀንን ምክንያት በማድረግ የተዘጋጀው ዓውደ ርዕይም ሀሳብና በጅምር ያለ የፈጠራ ሥራ ያላቸው ወጣቶች የተገኙበት ነው። በጅምር ያለ የቴክኖሎጂ ፈጠራ ሥራ ደግሞ ከፍተኛ ፋይናንስ የሚጠይቅ በመሆኑ የተለያዩ ባለሃብቶች አብረው እንዲሰሩ ለማድረግ ሥራዎችን ማሳየት የሚቻልበት አጋጣሚ መፈጠሩ በጎ ጅምር ስለመሆኑ ይናገራል።

ወጣት አበበ ነጋሽ ሌላኛው በዚህ አውደርእይ ሥራዎቻቸውን ይዘው ከቀረቡ ወጣቶች መካከል አንዱ ነው። የተለያዩ የዕደ ጥበብ ሥራዎችን የሚሰራው ወጣቱ በአይነስውርነት ያልተገደበ የብዙዎች ምሳሌ ነው።

ለንፅህና አገልግሎት የሚውሉ መጥረጊያና መወልወያ እንዲሁም የቤት ውስጥ ምንጣፎችን የሚሠራው አበበ ለዚህ ሁሉ ሥራ ምክንያት የሆነው በትውልድ አካባቢውም ሆነ በሀገሪቱ አካል ጉዳተኞችን በተመለከተ ያለው አመለካከት እራስን ካለመቻል እና ከልመና ጋር የተያያዘ በመሆኑ አካል ጉደተኛም እንደማንኛውም ሰው መሥራት የሚችል መሆኑን ለማሳየት ነው ይላል።

``ምንጣፍና መወልወያ መሥራት ከባድ አይደለም። ከዚህ በላይ የኤሌክትሪክ ሁሉ ብልሽት ሲገጥመኝ እንደማንኛውም አይናማ ሰው በቀላሉ ማስተካከል እችላለሁ’’ የሚለው አበበ በተጨማሪም በትውልድ አካባቢው የእንጀራ ምጣድ፣ ስቶቭ ጥገና የመሥራት ልምድ ስላዳበረ በርካታ ስራዎችን የመስራት ክህሎት እንዳዳበረ ይናገራል።

ሥራችንን በተመለከተ ብዙዎች የሚሰጡት አስተያየት አበረታች ነው የሚለው አበበ፤ ከዚህ የበለጠ ጠንካሮች እንድንሆን የሚያበረታታ አስተያት ይደርሰናል ይህ ከዚህ ቀደም አካል ጉዳተኞች ከሰው በታች እንደሆኑ ተደርጎ የሚወሰደው አመለካከት ከግዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ ስለመምጣቱ የሚያመለክት ነው ይላል።

የመንግሥት ድጋፍ በተመለከተ አበበ ሲናገር፤ ‹‹አካል ጉዳተኞች መበረታታት አለባቸው ምክንያቱም መንግሥትም የሚፈልገው ሥራ ፈት ወጣት እንዳይኖር ነው። ከዚህ አኳያ መንግሥት በተለያዩ ድጋፎች ከጎናችን ቢሆን ማንኛውም ሰው መሥራት እንደሚችል ምሳሌ ከመሆን ባለፈ ይበልጥ ተጠቃሚ እንድንሆን ያግዛል›› ይላል።

``ሰው ሥራ አጣሁ፤ ይላል ግን ሥራ ፈጣሪ መሆን ያለበት እራሱ’’ ነው የሚለው አበበ ‹‹መንግሥትን መጠየቅ የሚቻለው የመስሪያ ቦታ፣ የድጋፍ አገልግሎት ነው። ሥራ ፍጠሩልን ብሎ መንግሥትን መጨቅጨቅ ልክ ነው ብዬ አላምንም። ከመንግሥትም ቢሆን ድጋፍ ለማግኘት የሚታይ ነገር መሥራት ይጠይቃል። ስለዚህ ተቀምጦ ማማረር ሳይሆን መፍትሄው እራስን ለሥራ ዝግጁ ማድረግ ነው›› ይላል።

‹‹ሰዎች ምርታችንን በብዛት እየተጠቀሙ ነው›› የሚለው አበበ፤ በተለያዩ መልኩ ምርቶቻቸው የማስተዋወቅ ሥራ እንደሚሰሩ በዚህም ሕብረተሰብ ከተመሳሳይ ምርት ጋር አነፃጽሮ የእነሱን ምርት እንደሚገዛ ይናገራል። በጥራት እና በተመጣጣኝ ዋጋ መስራት ከተቻለም የገበያ ችግር እንደማያጋጥም ያስረዳል።

አሁንም የገበያ ትስስሩ አነስተኛ ስለሆነ ገበያ ያለበት አካባቢ የመሸጫ ሼዶች በመንግሥት ተመቻችተው ቢሰጡን የበለጠ ምርታማ ሆነን መውጣት እንችላለን የሚለው አበበ፤ የመሸጫ ሼዶች መኖር በስፋት ወደ ገበያ ለመግባት እንደሚያስችል ይናገራል።

‹‹የፕላስቲክ ደረቅ ቆሻሻ መጥረጊያ ቶሎ የሚሰበር በመሆኑና በአንፃሩ የእኛ ምርት በጥንካሬው የሚታወቅ በመሆኑ ሕብረተሰቡ በስፋት ጥቅም ላይ እያዋለ ነው የሚለው›› አበበ፤ መጥረጊያው ቢሰበር መልሰው አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጎ እድሳት ስለሚደረግለት የበለጠ በሕብረተሰቡ ዘንድ ተመራጭ ለመሆን እንዳበቃው ይናገራል።

‹‹አይነስውር ብሆንም ሥራውን በብቃት መሥራት እንደሚችል ለሁሉም ማሳየት ችያለሁ›› የሚለው ወጣት አበበ፤ በተለያዩ የሙያ መስኮች ያለውን አቅም ለማሳደግና ተጨማሪ አቅም ለመገንባት በትምህርት እራሱን ለማሻሻል መደበኛ ትምህርቱን እየተከታተለ እንደሚገኝ ተናግሮ በተለይ ለኤሌክትሪክ ጥገና የሚያስፈለገውን መስፈርት ለማሟላት ጥረት እያደረገ ስለመሆኑ ይናገራል።

ወደፊት የአካል ጉዳተኞች የሙያ ማሰልጠኛ ተቋም መመስረት እፈልጋለሁ የሚለው አበበ፤ ለዚህ እቅድ መሳካት ራሱን በተለያየ መልኩ ለማሳደግ ጥረት እያደረገ ስለመሆኑ ተናግሮ፤ የሚመለከታቸው አካላት በሚያስፈልገው ነገር ሁሉ ከጎኑ ቆመው ለብዙዎች ብርሃን የመሆን ሕልሙን እንዲደግፉ ጥሪውን ያቀርባል።

ስኬታማ ኧንተርፕረነሮች ከዛሬው እንቅፋት፣ ውጣ ውረድ ወይም ጊዜያዊ ድል ይልቅ የወደፊቱ ጊዜና የሚደርሱበት ከፍታ የሚታያቸው ናቸው የሚሉት ወጣቶቹ፤ ሁልጊዜም ከወራት፣ ከዓመታት በኋላ ሥራችን የት እንደሚደርስ በማሰብ ታትረው መስራት እንደሚገባቸው ይመክራሉ።

ወጣቶች ዛሬ በሚያጋጥማቸው እንቅፋት ሳይሰናከሉ ነገን ወደፊት አሻግረው በማየት በአሸናፊነት መንፈስ ሊጓዙ እንደሚገባም ስራ ፈጣሪ ወጣቶቹ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

## የምድር በረከት

# በማዕድን ዘርፍ ዳታ በማመንጨት ቀዳሚው ኢንስቲትዩት

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ኢትዮጵያ በማዕድን ሀብቷ የበለጸገች ሀገር ብትሆንም ቀደም ባሉት ጊዜያት ይህንን ሀብቷን ጥቅም ላይ በማዋል ረገድ የተሰሩ ሥራዎች እምብዛም አልነበሩም። ይሁንና አሁን ለኢኮኖሚ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ ተብለው ከተለዩት አምስት ዘርፎች አንዱ ሆኗል። በመሆኑም በዘርፉ መሻሻሎችና ለውጦች እየታዩ ነው።

እንደ ሀገር ያሉትን ማዕድናት ጥቅም ላይ በማዋል ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዲያስገኙ ከማድረግ አኳያ ዘርፈ ብዙ ሥራዎች እየተሰሩ ነው። በተለይ በማዕድን ዘርፍ በሚሰሩ ተቋማት አማካኝነት የማዕድናት አለኝታ ቦታዎች በመለየት በዘርፉ ለመሰማራት ለሚፈልጉ ባለሀብቶች ምቹ ሁኔታዎች ለመፍጠር የሚያስችሉ በርካታ ሥራዎች እየተሰሩ ነው። በዚህ ዘርፍ ከሚሰሩት ተቋማት መካከል የረጅም ጊዜ ልምድ ያካበተው የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት ተጠቃሽ ነው፡፡

ኢንስቲትዩቱ በአዋጅ በተሰጠው ስልጣንና ተግባር መሠረት የማዕድናት አለኝታ ቦታ በመለየትና ዳታ በማመንጨት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል። ኢንስቲትዩቱ የረጅም ጊዜያት ልምድ ያለው እንደመሆኑ በአገሪቱ የሚገኙ ማዕድናት ላይ ጥናት እያደረገ የአለኝታ ቦታ በመለየት የሰበሰበውን ዳታ በዘርፉ ኢንቨስትመንት ለመሳተፍ ለሚፈልጉ አካላት እየሰጠ ይገኛል።

አቶ ኢጃራ ተስፋዬ የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ናቸው። እሳቸው እንደሚሉት፤ ኢንስቲትዩቱ የተቋቋመው በእ.ኤ.አ 1968 ነው። የተቋቋመበት ዓላማ በዋናነት የሥነ ምድር መረጃን ማመንጨት ነው። የሥነ ምድር መረጃ ስንል የማዕድን ፍለጋ፣ የጂኦተርማል፣ የሥነ ምድር አደጋ እና የመሳሳሉት ሥራዎች ላይ የተለያዩ ማጥኛ ዘዴዎች ተጠቅሞ ያጠናል። ጥናቱ ሲጠናቀቅ የተገኘው ዳታው ለሚመለከተው አካላት ይሰጣል። በተጨማሪም የማማከር ሥራንም ይሰራል። እንዲሁም አብዛኞቹ አገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ማዕድናትና ማዕድንነክ ምርመራዎች የላብራቶሪ አገልግሎትም ይሰጣል።

ኢንስቲትዩቱ ዘርፈ ብዙ ስራዎችን ይሰራል። በተለይ በማዕድን ዘርፉ ቀዳሚ አድርጎ ትኩረት ሰጥቶት እየሰራ ያለው አገሪቱ ማዕድኑ እያላት ከውጭ የምታስገባው የማዕድናት ውጤቶች ላይ ነው። ይህም ከውጭ የሚገቡ የማዕድናት ውጤቶችን በሀገር ውስጥ የመተካቱ ሂደት በመንግሥት አቅጣጫ ተይዞ እየተሰራበት መሆኑን ዋና ዳይሬክተሩ ያመላክታሉ፡፡

ኢትዮጵያ ብዙ አይነት ማዕድናት ይኑራት እንጂ እስካሁን ባለው ሁኔታ ሀብቱን በሚፈለገው ልክ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችሉ ሥራዎች አልተሰሩም የሚሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በዚህ የተነሳ እስካሁን አገሪቷ ማዕድኑ እያላት ከውጭ የማዕድናት ውጤቶችን በማስመጣት እየተጠቀመች እንደምትገኝ ይገልጻሉ። አገሪቷ ከውጭ የምታስመጣው ማዕድኑን ሳይሆን ፕሮሰስ የተደረገው የማዕድን ውጤት መሆኑንም ይገልጻሉ። ለአብነትም ብረት፣ ማዳበሪያ፣ ማርብል፣ የድንጋይ ከሰል፣ ሴራሚክን እና ሌሎች ማዕድናት መጥቀስ ይቻላል፡፡

ዋና ዳይሬክተሩ እንዳብራሩት፤ የኢንስቲትዩቱ የማዕድን ዘርፍ ዋንኛ ሥራም ከውጭ የሚገቡ ኢንፖርት የሚደረጉ ምርቶች ላይ መሠረት ያደረገ ነው። ይህም ሲባል የመጀመሪያው ከውጭ የሚገቡ ምርቶች በሀገር ውስጥ ለመተካት የሚያስችል ዳታ ማመንጨት ነው። ዳታ ከመነጨ በኋላ በዘርፉ ለመሰማራት የሚፈልግ ኢንቨስተሮች ከሠሩበትና ፕሮሰስ ከተደረገ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ መተካት ያስችላል። ሁለተኛው አሁን ላይ ዓለም ያመጣቸው ወይም እያነሳቸው ያለው ዋነኛ ማዕድናት/ ክሪቲካል ሚኒራል/ የሚባሉ አሉ። እነዚህ አሁን ላይ ዓለም አቀፍ ደረጃ የሚፈልጉና ትኩረት ተደርጎባቸው የሚሰራባቸው ማዕድናት ላይ ኢንስቲትዩቱም እንደ ሀገር ትኩረት ሰጥቶት እየተሰራ ነው።

ለአብነት መኪና ብንመለከት በነዳጅ መጠቀም ትተን ወደ ኤሌክትሪክ መቀየር እንደማለት ነው። ወደ ኤሌክትሪክ ሲቀየር ደግሞ ሊትየም፣ ኮባልት፣ ግራናይት፣ ኮፐር እና የመሳሰሉ ማዕድናት ያስፈልጋሉ። በአሁኑ ወቅት ደግሞ አብዛኛዎቹ የኤሌክትሪክ መኪና ወደ ኢትዮጵያ እየገቡ እንደመሆናቸው መጠን የእነዚህ መኪኖች አካላት ሆነ ባትሪ ለመስራት የማዕድን ውጤቶች ጥቅም ላይ የሚውሉ መሆኑን ጠቅሰው፤ እነዚህ ዓለም ትኩረት ያደረገባቸው ማዕድናት ላይ ለመስራት ጥናት እየተደረገ መሆኑንም ያስረዳሉ፡፡

ሦስተኛው ደግሞ መቼም ቢሆን ፍላጎቱ የማይቆም ማዕድን አይነት አለ። ለምሳሌ፤ እንደ ወርቅ አይነት ማዕድን፤ ይህንንና ሌሎች መሰል ማዕድናት ላይ ጥናት ያደረጋል። ኢንስትቲዩቱ በማዕድናት ላይ የሚሰራቸውን ሥራዎች በእንደዚህ መልኩ ከፋፍሎ እየሰራ መሆኑን ዋና ዳይሬክተሩ ያብራራሉ።

ኢትዮጵያ ብዙ ማዕድናት አይነቶች እንዳሉት ቢታወቅም ነገር ግን ጥልቀት ያላቸው ጥናቶች አልተጠኑም ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ይህ እንዳይሆን ያደረጉት ምክንያቶች ብዙ ቢሆንም ከእነዚህ መካካል ቀደም ባሉት ጊዜያት የማዕድን ዘርፉ ትኩረት ተነፍጎት የቆየና ብዙ ኢንቨስት ያልተደረገበት መሆኑ በዋናነት ያነሳሉ። ዘርፉ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ግን ትኩረት አግኝቶ ከአምስቱ የኢኮኖሚ ዘርፎች አንዱ መሆኑ ጥሩ መስመር እንዲይዝ ያደረገው መሆኑን ያመላክታሉ። ‹‹የማዕድን ዘርፉ ትኩረት አግኝቶ ሥራዎች እየተሰራበት ነው ስንል ብዙ ተግዳሮቶች ከፊታችን አሉ። ተግዳሮቶች ቢኖሩም የምንወጣቸው ናቸው›› ይላሉ።

በማዕድን ዙሪያ ምን ተሰራ ብለን ስንጠይቅ እዚያ ቦታ ላይ በዚህ ያህል መጠን እንደዚህ አይነት ማዕድን አለ የሚለው በደንብ መታወቅ አለበት። ይህንን ለማድረግ ደግሞ ጅምር ሥራዎች ቢኖርም ገና ብዙ አይነት ጥናቶች ያስፈልጋሉ። አንድ ቦታ ላይ ያለን ማዕድን ለማወቅና ለመለየት ከመጀመሪያ እስከመጨረሻው ድረስ ዘርፈ ብዙ ጥናቶች ይደረጋሉ፤ በዚያው ልክ ወጪውም ብዙም ነው። ይህም ደግሞ በጀት፣ የተማረ ሰው ኃይል እና ሌሎች ነገሮችን ይፈልጋል። እነዚህ ነው ከሰራን ብዙ ስራዎች መስራት ይቻላል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ቀደም ባሉት ጊዜያት የተሰሩ የተወሰኑ ስራዎች ቢኖሩም ኢትዮጵያን የሚመጥን ሥራዎች ተሰርተዋል ማለት አይቻልም፤ ያሉት ጥናቶች በጥልቀት ያልተጠኑ ውስን ናቸው›› የሚሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ዘርፉ ትኩረት ከተሰጠ በኋላ ግን በተመረጡና ወሳኝ በሆኑ ማዕድናት ላይ ብዙ ሥራዎች ለመስራት ታቅዶ እየተሰራ መሆኑን አስታወቀዋል፡፡

እንደ እሳቸው ማብራሪያ፤ ኢንስቲትዩቱ በ50 ዓመታት እድሜ ውስጥ በርካታ የሥነ ምድር ዳታዎች አመንጭቷል። የማዕድናት አለኝታ ቦታዎች ከመለየት አኳያ ሰፊ ሥራዎች ተሰርተዋል። የከበሩ ማዕድናት ብዙ አለኝታ ቦታዎች ተለይተዋል። የባሕላዊ ወርቅ አመራረት ላይ ጥናቶች ተጠንተዋል፤ ብዙ ምርትም ተገኝቷል። የጂኦተርማል የአለኝታ ቦታዎች በጥናት ተለይተዋል።

በ2016 በጀት ዓመት በማዕድን ዘርፍ በርካታ ሥራዎች ተሰርተዋል። የኢንስቲትዩቱ የሥነምድር ዳታን ያመነጫል ሲባል የተቋሙ ባለሙያዎች በየመስኩ በመገኘት ጥናትና ምርምር ያደርጋሉ፤ ናሙናዎቹ ተሰብስበው ላብራቶሪ ገብተው ትንተና ከተሰራላቸው በኋላ ተገምግሞ ሪፖርቱ ይዘጋጃል። በዚህ ሂደት ዘንድሮ የተጀመረው ሥራ ሪፖርቱ በሚቀጥለው ዓመት ነው የሚደርሰው። ምክንያቱም በዘንድሮ ዓመት መስክ ተወጥቶ ናሙናዎች ተሰበስበው ላብራቶሪ ይገባሉ፤ ከዚያ አስፈላጊውን ሂደቶች ጠበቆ ስለሚሰራ ረጅም ጊዜያትን ሊፈጅ ይችላል ሲሉ አስረድተዋል።

በዚህ መሠረት በዘንድሮ ዓመት የተጀመረው ሥራ ሪፖርት የሚደርሰው በሚቀጥለው ዓመት በ2017 ነው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በዘንድሮ ዓመት ብዙ ክልሎች ላይ የድንጋይ ከሰል፣ የደለል ወርቅ፣ የኒኬል ማዕድን፣ የኢንዱስትሪያል ማዕድን፣ የሊትየም እና የብረት ማዕድናትን የአለኝታ ቦታ ልየታ መስራቱን ያመላክታሉ። በተያዘው በጀት ዓመት በተለያዩ ክልል የጂኦሎጂ ካርታ፣ ጂኦኬሚስትሪ ጥናት፣ የሥነ ምድር አደጋ፣ የጌጣጌጥ ማዕድናት፣ እና ጂኦተርማል የአለኝታ ቦታ መካሄዱንም ይገልጻሉ። የአለኝታ ቦታ ልየታ ከተሰራባቸው ክልሎች መካካል ሲዳማ ክልል የደለል ወርቅ፣ ጅማ ዞን የድንጋይ ከሰል፣ ደቡብ ክልል ምዕራብና በጋምቤላ ክልል የኒኬል ማዕድን፣ ሐረርና ምስራቅ ሐረርጌ ኢንዱስትሪ ማዕድን፣ ድሬዳዋ አካባቢ ሊትየም ማዕድን፣ ሱማሌ ክልል እና ምስራቅ ሐረርጌ አካባቢ፣ ብረት ማዕድን፣ ደቡብ ምዕራብና ጋምቤላ አካባቢ ክሮማይት፣ ደቡብ ኢትዮጵያ ጌጣጌጥ ማዕድን ላይ መስራቱን አስታውቀዋል።

የጂኦፊዚክስ ምርምር በድሬዳዋ አካባቢ፣ የጂኦተርማርል ሲዳማ ክልል እንዲሁም ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መሰል ሥራዎች ተሰርተዋል። የጂኦተርማል ሰፋ ያለ ቦታዎች የያዘ መሆኑን ገልጸዋል። በእነዚህ በተጠቀሱት ቦታዎች ላይ የተገኙት ማዕድናት ዳታዎች ተሰብሰበው የላብራቶሪ ውጤታቸው እየወጣ ሪፖርታቸው እየተዘጋጀ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

በኢትዮጵያ በማዕድን ዘርፉ ኢንቨስት ለማድረግ የሚፈልጉ ባለሀብቶችና ተቋማትም በሁሉም የአገሪቷ አካባቢዎች ቢሰማሩ ብዙ መልካም እድሎች እንዳለሉ የጠቆሙት ዋና ዳይሬክተር፤ በአገሪቱ ብዙ ጥልቅ ጥናት ስላልተጠና ብዙ የማዕድን ሀብት እንዳልወጡ ያመላክታሉ። እሳቸው እንደሚሉት፤ የኢትዮጵያ ጂኦሎጂ ጥናቶች የሚያመላክቱት የማዕድን ሀብት ክምችት በታወቁ ቦታዎች አሉ። በአገሪቷ ሰሜን፣ ምዕራብና ደቡብ አካባቢዎች በአብዛኛው የወርቅ፣ ብረት እና ሌሎች ይገኛሉ። በምስራቅ አካባቢ ደግሞ በአብዛኛው የግንባታ ማዕድናት የሚገኝ ሲሆን፤ በመሀል አገር የኢንዱስትሪ ማዕድናትና የከበሩ ማዕድናት ይገኛሉ ።

ስምጥ ሸለቆም እስከ 10ሺ ሜጋ ዋት ጂኦተርማል ኃይል ማመንጨት የሚያስችል ሲሆን፤ ሰሜን አካባቢ የትግራይ አካባቢ የከበሩ ማዕድናት፣ ወርቅ እና ሌሎች ማዕድናት ይገኛል። የአፋር ክልል ጂኦተርማል፣ ፖታሽና ሌሎች በርካታ ማዕድናት አሉ። የሱማሌ ክልልም እንዲሁ ነዳጅ እና ሌሎች ማዕድናት እንዳሉት ይታወቃል።

በሌላ በኩል ኢንስቲትዩቱ በአገሪቱ ውስጥ በማዕድን ዘርፉ ላብራቶሪ አገልግሎት በመስጠት ቀዳሚ የሆነ የማዕድን ላብራቶሪም እንዳለው ዋና ዳይሬክተሩ ይገልጻሉ። ይህ ላብራቶሪ ለራሳቸውና ለውጭ ተጠቃሚዎች አገልግሎት እንደሚሰጥ ይጠቅሳሉ። ቀደም ባሉት ጊዜያት ላብራቶሪው በማዕድን ዘርፉ በምስራቅ አፍሪካ አሉ ከተባሉት ላብራቶሪዎች መካከል አንዱ እንደነበር ጠቅሰው፤ ዘርፉ ትኩረት ተነፍጎት በመቆየቱ የተነሳ በየጊዜ እየተዳከመ መምጣቱንና ድሮ ከነበረበት መውረዱን አልሸሸጉም። ያም ቢሆን ታድያ እንደገና በማደራጀት ብዙ ሥራዎች እየተሰሩ እንደሆነ አመላክተዋል። “አሁንም ቢሆን በላብራቶሪ ውስጥ ብዙ ሥራዎች ይሰራሉ። ለምሳሌ ያህል ኢትዮጵያ የምትገዛው ብሔራዊ ባንክ የሚገባው ወርቅ በዚህ ላብራቶሪና በቅርንጫፍ ባሉ ላብራቶሪዎች አማካኝነት በመሆኑ ላብራቶሪው አይተኬ ሚና አለው” ይላሉ።

በላብራቶሪው ብዙ አይነት ምርመራ እንደሚሰጥ የጠቀሱት ዳይሬክተሩ፤ ላብራቶሪ እንደ ድሮ አይደለም፤ መሳሪያዎቹ እያረጁ ስለሆኑ የሚጠቀሙባቸው ኬሚካሎችም ሆነ መሳሪያዎች እና ሌሎች ግብዓቶች ኢምፖርት የሚደረጉ ናቸው ብለዋል። ይህ ደግሞ ትልቅ ተግዳሮት ሆኖ ቢቆይም አሁን ላይ ተስፋ ሰጪ ነገሮች እየታዩ መሆኑን አመላክተዋል። መንግሥትም ትኩረት ሰጥቶት እየተሰራ በመሆኑ ላብራቶሪውን የማዘመን ሥራ እየተሰራ መሆኑን አስገንዝበዋል።

ኢንስቲትዩቱ በማዕድን ዘርፍ የሚሰራቸው አብዛኞቹ ሥራዎች የመስክ ሥራዎች በመሆናቸው የበርካታ አጋር አካላት ተሳትፎና ትብብርን ይጠይቃል። በዚህ የተነሳ ብዙ ችግሮች ያጋጥማሉ ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ለአብነትም የሰላም ሁኔታን አንስተዋል። በቂ የሆነ ተሽከርካሪዎች አስፈላጊ እንደሆኑም ጠቅሰዋል። የሠራተኞች ፍልሰት፣ ኢንፖርት የሚያደርጉ ኬሚካሎች፣ የመመርመሪያ መሳሪያዎች፣ መለዋወጫ ያለመገኘት እና የመሳሳሉት ተግዳሮቶች ይጠቅሳሉ። አሁን ላይ ለዘርፉ ትኩረት ስለተሰጠው ጥሩ ተስፋ ሰጪ ነገሮች እየታዩ መሆኑን ጠቅሰው፤ እነዚህን ተግዳሮቶች ለመቅረፍ እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች ስላሉ ችግሮቹ በአጭር ጊዜ የሚፈቱ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

የኢንስቲትዩቱ የማይነካው ዘርፍ የለም፤ ማዕድን፣ ኢነርጂ፣ ቱሪዝም፣ ውሃ፣ ግንባታ እና መሰል ዘርፎች ይነካል የሚሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ እንደተቋም በቀጣይ የተያዘው አቅጣጫ ደግሞ ከዓለም ጋር አብረው መሄድ የሚጠይቅ ነው። ምክንያቱም ዓለም የሚፈልጋቸው ማዕድናት ላይ እንደ ሀገር የሚሰሩ ሥራዎች መኖራቸው ይጠቅሳሉ። የመጀመሪያው ግን ኢንፖርትን የሚተኩ ማዕድናት ቅድሚያ በመስጠት የሚሰራባቸው ሲሆኑ፤ አገሪቷ ማዕድኑ እያላት ኢንፖርት የምታደርጋቸው የማዕድናት ውጤቶች ላይ ዳታ በማመንጨት ሥራ የሚሰራ መሆኑን አመላክተዋል።

ሁለተኛ በየጊዜው የማዕድን ፍላጎት ይቀያየራል። የዓለም አገራት አሁን ላይ የሚፈልጉት ማዕድናት ላይ እንደ ሀገር ደግሞ ዳታ በማመንጨት ሥራዎች ይሰራሉ። በጂኦተርማል፣ በሥነምድር አደጋዎች ላይ አስፈላጊ የሆኑ ሥራዎች ይሰራሉ። ይህ ሁሉ ሥራ እንዳለ ሆኖ ኢትዮጵያ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ በማውጣት ወደ ሀገር ውስጥ በምታስገባቸው ማዕድናት ላይ በትኩረት ይሰራል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

በተጨማሪም አሁን ላይ የአለኝታ ቦታ ልየታ እየተሰራ መሆኑን ጠቅሰው፤ የተወሰኑ አቅም ወይም ኃይል በማሰባሰብ ወሳኝ ወደ ሆነው የክምችት ግምት የሚገባቸው የማዕድን አይነቶች መኖራቸውን ገልጸዋል። በሌላ በኩል ኢንስቲትዩቱ በማዕድን ዘርፉ የሚሰበሰቡ ዳታዎችን መረጃ ለሚፈልጉ የተለያዩ አካላት እያሰራጨ መሆኑን ዋና ዳይሬክተሩ አስታውቀዋል።



የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ ኢጃራ ተስፋዬ፤

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## አንቀልባ

**ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሽከታብ)**

**ባሳደኩ..**

ትላንትን ካላስረሳ ማደግ ምን ሊረባ?

ኖዎር እና ነውር..በሕይወት ግርግም ስር ምንና ምን ናቸው?

..........

አስራ አምስት ቀናት በምድር ላይ አልነበርኩም። አንዳንዴም ከዛ እሰነብታለሁ። ከሕልሜ ስንሸራተት፣ በፍኖተሎዛ አሸልቤ እንዲያዕቆብ የወርቅ መሰላል አላይ ስል፣ ተስፋ ያደረኩት ሲርቀኝ..ራሴን ድራሼን አጠፋዋለሁ። ራሴን ስሰውር ማንም አያስተውለኝም። ውሀ አጣጬ የወርቅ ውሃም ብትሆን አታውቀኝም።

‹አስተውለሽ ከሆነ ያልነበረውን እኔን ነበር ስታቅፊና ስትዳሪው የሰነበትሽው› ብላት ምን እንደምትመለስ ባላውቅም ለመቼም የማይፀዳ ግርታን ግን እጠብቃለሁ። እንደሰው ነኝ እኮ! ግን በከፊል አቅሌን ስቼ ነው።

በሕልሜ የተሳለ ልደርስበት የምሻው ግን ያልደረስኩበት የሆነ ስፍራ አለኝ። መንገዶቼ በሳማና ጋሬጣ ሲከለሉ የማልደርስበት እየመሰለኝ እላሽቃለሁ። ያኔ እሰወራለሁ..ድምጥማጤን አጥፍቼ ኃይል አሰባስባለሁ።

ወደመሮጫ ትራካችን ያገጠጡ ብዙ የድካም ጨረሮች አሉ። ከነዛ ጨረሮች መሐል አንዱ ሲጨርፈኝ ራሴን እሰውራለሁ። ከሰው መሐል በሀሳቤ እርቃለሁ። ከቤቴ፣ ከትዳሬ፣ ከግዛቴ ሸሽቼ አንባ እጠጋለሁ። ሀሳብ መደበቂያ ዋሻ ነው። ሀሳብ ሀገር ነው..ከዚህ ወደዛ ማቅኚያ። ራስን በሕልም ውስጥ እንደመሰወር የፅድቅና ገዳም አለ ብዬ አላስብም። ወዴትም ሳላገድም ከምርጦቼ አንዱ ወደሆነው ተስፋዬ እንፏቀቃለሁ። ልክነት እስኪጎበኘኝ ድረስ በሕልሜ ሸንቁር ውስጥ አጮልቃለሁ። ሰንኮፌን ገፍፌ ብቁ ስሆን በሄድኩበት መንገድ ወደጎጆዬ እመለሳለሁ። ከዝምታ፣ ከሸሽታ ወደ ሕይወት..

ጣሪያዬን ሸንቁሬ ጨረር አልናፍቅም። በሬንና መስኮቴን እከፍታለሁ እንጂ። ልባችን ለግሞ እንጂ አልከፈት ያለ በርና መስኮት የለም። በሬን ኦና አድርጌ ንፋስ አላስገባም..ጓዳዬን አላስቃኝም። በንፋሱ ልክ በሬን እገረብባለሁ እንጂ። ጨረቃን ለማየት በቀን አላንጋጥጥም ሲመሽ እወጣለሁ እንጂ። ፀሐይን ለመሞቅ በምሽት አልባዝንም እኩለ ቀንን እጠብቃለሁ። ለፈካ ብርሃን ላምባዬን አልደፋም..ኩራዜን አልሰብርም መላ እዘይዳለሁ እንጂ።

ያለቦታችን ቦታ የለንም። የቆምንበት የእኛ ካልሆነ እንሸራተታለን። የእኛ ከሆነ ደግሞ ማንም አይገፋንም። ለፊት ለፊት ከሆነ የታጨነው ከኋላ ብንቆም እንኳን ወደፊት መምጣታችን አይቀሬ ነው። ኋለኞች ከሆንም ፊት ብንገተርም ማፈግፈጋችን ያመነ ነው።

..........

**አንቀልባ የሕይወት ከፈኔ...**

ከተፈጥሮ ኩሬ ስር በደም እርጎ ስንፎለፎል፣ እንደመሐረብ ለገላዬ የተሰጠኝ ብጣቂ ጨርቄ ላይ ሕልሜ ታትሞበታል። በቀራንዮ በጨርቋ ላይ የጌታን ፎቶ እንዳስቀረችው ቬሮኒካ ምስሌ ቀርቷል። በማርያም ስም፣ በእልልታ በእናቴ ደረት ላይ በልጅነት ሳርፍ የነበረውን እያለምኩ ማደግን ጠላሁት። እስካልገባን ድረስ ልጅነት ነውራችን ነው እስከገባ ድረስ ማደግ ውርደታችን ነው። የሕይወትን አሳማሚ አርጩሜ ወደንና ተገደን የምንቀምስበት የቅጣት ክፍለዘመናችን ነው..ማደግ።

በብርሃን ሸርጥ አንዳንዴም በጉም ባተቶ ታጅባ በምስራቅ ሸንቁር ስር ፀሐይ ትወጣለች..በምዕራብ ትጠልቃለች..ዓለም አዲስ ነገር የላትም። አዲስ ነገራችን ከእናታችን ጀርባ..ከእቅፏ ስር የቀረ ነው። ነፍስ ማወቅ በሚሉት ፀጋ ገፋፊ ብሂል ካጠላብን የተፈጥሮ ጥላ እየራቅን ወደተሲያት መንሸራተት። ዳዴ ማለትና በአትያዙኝ ስም ራሳችንን ችለን መቆም ስንጀምር የሚጀምር መከራ እንጂ ድሎት የለም።

ሕልማችን ልጅነታችን ጋ ቀርቷል..አብሮ ከስሟል። ከእናት ጀርባ ስንወርድ፣ አፋችንን በስድብ የፈታን እለት፣ ሰባት ዓመታችንን ስናከብር፣ ትምህርት ቤት ለመግባት ጆሯችንን ስንነካ ያኔ ላይመለስ ጥሎን ሸሽቷል። ለማቆጥቆጥ..ለመለምለም ሥራችን ህብስት አልቀበል እስኪለን ድረስ ዳክረናል። ችግር፣ መከራ፣ መውጣት መውረድ፣ ረሀብ እርዛት ከሸንቋጤአቸው ጋር እስኪተዋወቁን ድረስ ከአንቀልባ ወደባቅላባ የሁሉም ሰው ምኞት ነው። ማደግ እፎይን ካልሰጠን አለማደግ በስንት ጣሙ?

ከመከራዬ ለማምለጥ የእናቴን ጉያ እሻለሁ...ከነምናምኔ ውሸቅ ማለት። የሆነ እለት ሌሎች ሀሳባችንን ወርሰውልን ሀሳብ አልባዎች ነበርን። የሆነ እለት በእኛ በገዘፉ ተጠለን ተሲያት አልነበረንም። ዓለማችን በዓለማቸው ተሰፍቶ ዓለም የለሾች ነበርን። በማደግ ስም ከሰነበትንበት ጉያ ወጣን..ያን እለት ፀሐይን ተዋወቅናት። ዓለምን ዋጀናት። ተፈጥሮን ለመድናት..ከነመከራቸው።

ረሀባችንን ተርበው፣ ትካዜያችንን ተክዘው ነፃ ያወጡን ግዙፎች ዛሬም አሳቢያችን ቢሆኑም እንደያኔያቸው በልካቸው ሊያበጁን ግን የታደሉ አይደለም። በማደግ ስም እንቢታን ወርሰናል..በዘመን ስም ሀፍረትን ተከናንበናል። በተፈጥሮ በኩል ሌላ መልክን ተዋወቅናል። ለማንም የማይጋሩ ስሜትና ስሌት ሰለባዎችም ነን። ስለሆነም ድሮን ናፋቂ ቀኝ ዘመም ሕልመኛ ነኝ።

ልጅነቴ ጀምሮ ያበቃበት እሱ ስፍራ ሕይወቴ ጀምሮ ያበቃበት ነው። ዳዴ እንደከዳቸው እንደአራስ የዶሮ ጫጩት ከሸሌ ውስጥ ራሴን ፈልፍዬ እናቴ ጀርባ ላይ ማስቀመጥ ያምረኛል። ለመኖር ከንፋቸው እንዳልጠና ተንደፋዳፊ እፆች በእንፋቅቄ ሄጄ ሕልሜን ማስመር እንዲሁ። በልጅነት ልቤ ከጎዋ ተገንጥለው ወደቤት ሲያጮለቁ የማያቸው እነዛ የብርሃን ፍርግርጎች..አግድም ዘንበው የቤታችንን ለዋገን ያራሱ ውሽንፍሮች..እንደሙዚቃ ቆርቆሮ ላይ ሲያርፉ የሚሞዝቁት የዝናብ ራሶች..ባላደግኩን ነፍሴ ላይ ያሳርፉብኛል።

ትላንት ከዛሬ ዘገር ማምለጫ ዋሻችን ነው። ባላደግን ከሚል ምኞት አሸሽቶ ወደጥንተ ቡረቃችን የሚጥለን። ባላደኩ የብዙ ሰው የአሁን እንጉርጉሮ ነው። በትካዜያችን ሰሞን የሚይዘን እጅ ሲጠፋ፣ ተስፋ ያደረግነው ሲከዳን ያን ዘመን እንናፍቃለን። በወፌ ቆመች መቆም ያለመደንን፣ መሄድ ያስቻለንን እጅና ልብ።

በእሽሩሩ መቀመጫዬን እየጠበጠበ ጀርባዋ ላይ ያስተኛኝ፣ ከማህጸን እኩል ውበት ባለው በሆነ ዓይነት የሙዚቃ ድምፀት ወደእንቅልፍ የሄድኩበት የአባብሎት ዜማ፣ ዛሬም ድረስ ያላባራሁትን መሻት ያስታቀፈኝ የፀጉሯ ሽርታቴ በሆነች ሴት ተቀይሮ እማዬን ቢያስረሳኝ..ድሮዬን ቢያስጠላኝ..ልጅነቴን ቢቀማኝ አሊያም በዛ ሕልሜ ምትክ እሽሩሩ ባይ ቢሰጠኝ የሚለው ከሰነበቱ ምኞቶቼ መሐል ቢሆንም ድሮን ከማለም አልታደገኝም። በዶቃና በዛጎል ያጌጠው፣ በተራመደች ቁጥር እየተቅጨለጨለ እንደእሽሩሩዋ የሚያጅበኝ የእቅፌ አንቀልባ የነፍሴ የሙዚቃ ባንድ ሆኖ ባላደኩኝ ያስመኘኛል።

የእናቴ የአደሷ ጠረን የተዋረሰበት አንቀልባዬ፣ ከእርምጃዋ እኩል እንደጽናጽል የሚቅጨለጨሉት እነዛ ዛጎልና ዶቃ ውሕድ ድምፆች.. ጀርባዋ ላይ በተነሰነሰ ፀጉሯ ላይ ተደላድዬ ተኝቼ፣ ዛሬም ድረስ በሚገርመኝ ብልሀት በግራ ጎኗ በኩል አሳልፋ ጭኖቿ ላይ አስቀምጣኝ በፀጉሯ ሰንበር ያወጣ ጉንጬን እየጠነቆለች ስትስመኝ...ከጡጦ ወደጡት እየተገላበጥኩ፣ ነጭ ሳቀረሻ፣ በልቼ እንዳጋሳ ጀርባዬን ስትመታኝ፣ ስቅታዬ እንዲተወኝ አናቴ ላይ እፍ ስትልብኝ፣ የአናቴ ትርትር አንዳች እንዳያርፍበት ስትሸሽገኝ..የእጆቼን መዳፍ ከጎኗ አርቃ ስሯ ስትገነድሰኝ የነበረውን የሚደልዝ..እንዳልነበረ የሚያደርግ ምን የዘመን ሞገስ አለ? ባላደኩ...

**ባሳደኩ..**

ማደግ ቅጣት ነው..በሥጋ ደልቦ በመንፈስ መኮሰስ። አለመወለድ እኩያ የሚሆነው ከመጥናት ጋር ነው። ነፍስ ማወቅ ነፍስ መሳት እንደሆነ ሳይገባን ማደግን እንናፍቃለን። ማደግ የብኩርና ፀጋን ገፎ ክፉና ደጉን የሚያሳውቅ ነው..መጨረሻው ግን እንደአዳምና ሄዋን ውለታ መብላት፣ በብዙ ርግማን ከርስት መፈንቀል ነው። አዳምና ሄዋን ኩነኔ ባልነካው በልጅ ሀሳብ ከክብር ጋር ነበሩ..አወቅን ባሉ ሰዓት የሀሳቦቻቸው አፎት ፈጃቸው። አፎቶቻችን ሀሳቦቻችን ናቸው..ቀንድ አውጥተው የሚወጉን፣ ጥርስ አውጥተው የሚነክሱን። ባላደኩ.. ከዘመን ባልተደባለኩ። ጊዜ አኩርፎኝ በበቀል ድሮ ላይ ቢወረውረኝ። እያቀረሻሁ፣ ሳላስብና ሳላመዛዝን፣ ክፉና ደጉንም ሳለይ እናቴ ሀሳብ ገነቴ ላይ በሰነበትኩ። ባላደኩ..

**ትላንትን ካላስረሳ ማደግ ምን ሊረባ?**

ማደግ መርሳት ነው..መርሳት ካልሆነ ግን ማደግ ማበድ ነው። ማደግ መፍራት ነው..ማፈር ነው..ካልሆነ ግን መዛል ነው። የዛሬ ቀለሞች የነገን ውበት ካልማረኩ..ካልሰወሩ..ካላደበዘዙ ወይም ካላስረሱ ማደግ መውደም ነው።

**ኖዎር እና ነውር..በሕይወት ግርግም ስር ምንና ምን ናቸው?**

ከእንግዲህ እንደልጅነታችን የምናቀረሽበት የእድሜ ወሰን የለንም። ሁሉም ጅላጅልነት በኖዎር ተቀይሯል። ኖዎር የማደጋችን ላቅ ሲልም የመብሰላችን ማረጋገጫ ነው። በነውር ቀይረን መደዴ ሲወጣን በሕይወት ግርግም ስል በትዝታ መሬት እንጭራለን።

ኖዎር የብስለት..ነውር ደግሞ የክስረት ማኅተሞች ሆነው ለእያንዳንዳችን የተሰጡን የእድሜ ዘውዶች ናቸው። ማፈርና መታፈር..

ልጅነቴ የሆነ መልክ ከሆነ ሀሳብ ጋ ስሏል። ዛሬም ድረስ የሚታየኝ ያ መልክና ሀሳብ ነው..

# ዓለም አቀፍ

## የዝንጀሮ ፈንጣጣን ለመከላከል የተገኘው ድጋፍ ከ10 በመቶ በታች ነው ተባለ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**




በአፍሪካ የተከሰተውን የዝንጀሮ ፈንጣጣ (ኤም ፖክስ) ስርጭትን ለመከላከል እየተደረገ የሚገኘው ጥረት ከፍተኛ የገንዘብ እጥረት እንዳለበት ታወቀ።

ተቋሙ በአሁኑ ወቅት በአሕጉሪቷ የተለያዩ አካባቢዎች ስርጭቱ እየጨመረ የመጣውን በሽታ ለመቆጣጠር የሚገኘው የፈንድ ድጋፍ ከክትባት ውድነት ጋር ተያይዞ እክል እንደፈጠረበት ገልጿል።

በአሁኑ ወቅት በሽታውን ለመከላከል አጠቃላይ ከሚያስፈልገው 245 ሚሊዮን ዶላር 10 በመቶውን ወይም 20 ሚሊዮን ዶላር ብቻ ማግኘቱን ያስታወቀው የአፍሪካ ሲዲሲ፤ ተጨማሪ የገንዘብ እና የክትባት ድጋፎችን በአፋጣኝ ማግኘት ካልተቻለ ስርጭቱ ሊከፋ እንደሚችል አሳስቧል፡፡

የአፍሪካ ሲዲሲ ዋና ኃላፊ ንጋሽ ንጎንጎ “በአሁኑ ወቅት ከአፍሪካ ኅብረት እና ከኮንጎ መንግሥት ባገኘነው 20 ሚሊዮን ዶላር እየተንቀሳቀስን እንገኛለን በሽታው እየሄደበት ከሚገኘው የስርጭት መጠን አንጻር ይህ እጅግ ዝቅተኛ ነው” ብለዋል፡፡

የድርጅቱ ዋና ዳይሬክተር ጄን ካሴያ በበኩላቸው አንድ ሚሊዮን ዶዝ ክትባቶችን በድጋፍ መልክ ለማግኘት የአፍሪካ ሲዲሲ በእንቅስቃሴ ላይ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

ፈረንሳይ፣ ጀርመን እና ስፔን ድጋፍ ከሚያደርጉ ሀገራት መካከል ሲሆኑ ሌሎች ክትባት አምራቾች እና ሀገራት ተጨማሪ ድጋፎችን እንዲያደርጉ በመጠየቅ ላይ መሆናቸውንም ነው የተናገሩት፡፡

የአውሮፓ ኅብረትና የኔዘርላንዱ የክትባት አምራች ባቫሪያን ኖርዲክ ለአፍሪካ የክትባት ድጋፍ ለማድረግ ቃል ገብተዋል፡፡

በጦርነት እየታመሰች ከምትገኘው ከዴሞክራሲያዊት ኮንጎ ተነስቶ ሌሎች የአሕጉሪቷን ሀገራት እያዳረሰ የሚገኘው የዝንጀሮ ፈንጣጣ በዓለም ጤና ድርጅት ማኅበረሰባዊ የጤና ስጋት ስለመሆኑ ለሁለተኛ ጊዜ ታውጇል፡፡

አፍሪካ በአሁኑ ወቅት ስርጭቱ በሚገኝበት ደረጃ በአጠቃላይ 10 ሚሊዮን ዶዝ ክትባት እንደሚያስፈልጋት ያስነበበው ሮይተርስ የክትባቱ ዋጋ ውድነት ፈተና መደቀኑን ዘግቧል፡፡ የክትባቱ አምራቾች በአሁኑ ወቅት የአንድ ዶዝ ክትባት ዋጋ 100 ዶላር ተምነው በመሸጥ ላይ ናቸው፡፡



## ሩሲያ በ92 አሜሪካውያን ላይ ማዕቀብ ጣለች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ሩሲያ በ92 አሜሪካውያን ላይ ማዕቀብ ጣለች።

የሩሲያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዳስታወቀው በ92 አሜሪካውያን ላይ ማዕቀብ ተጥሎባቸዋል።

ማዕቀብ የተጣለባቸው አሜሪካውያን ወደ ሩሲያ እንዳይገቡ፣ እንዳይሠሩ እና በሩሲያ ያላቸው ገንዘብ እንዳይንቀሳቀስ ታግደዋል።

ማዕቀብ ከተጣለባቸው አሜሪካውያን መካከል የዎልስትሪት ጆርናል፣ ኒዮርክ ታይምስ፣ ዋሽንግተን ፖስት እና ሌሎችም ዓለም አቀፍ ተፅዕኖ ፈጣሪ ሚዲያዎች ውስጥ የሚሠሩ ጋዜጠኞች አሉበት።

ከጋዜጠኞች በተጨማሪም የሕግ ባለሙያዎች፣ ተመራማሪዎች፣ ታዋቂ የንግድ ሰዎች እና የሙያ ማኅበራት አመራሮች ማዕቀቡ ተጥሎባቸዋል።

በአጠቃላይ ሩሲያ ወደ ግዛቷ እንዳይገቡ ማዕቀብ የጣለችባቸው አሜሪካውያን ቁጥር ከ2 ሺህ እንዳለፈ ቪኦኤ ዘግቧል።

ባሳለፍነው ሳምንት አሜሪካ ከዩክሬን ጦርነት ጋር በተያያዘ በ400 ሩሲያ እና ቻይናውያን ላይ ያነጣጠረ ማዕቀብ መጣሏ ይታወሳል።

ሩሲያም በአሜሪካ ለተጣለባት ማዕቀብ የአጸፋ እርምጃ የወሰደች ሲሆን ቻይና የዋሽንግተንን ማዕቀብ ከማውገዝ ባለፈ እስካሁን ተመሳሳይ ማዕቀብ ስለመጣሏ አልታወቀም።

ለአንድ ሳምንት በሚል የተጀመረው የዩክሬን-ሩሲያ ጦርነት ሦስተኛ ዓመቱ ላይ ይገኛል። ጦርነቱ በድርድር እንዲያልቅ በተለያዩ አካላት ጥረቶች እየተደረጉ ቢሆንም ጦርነት እንደቀጠለ ይገኛል።

የዩክሬን ፕሬዚዳንት ሩሲያን ወደ ድርድር ለማምጣት በሚል በምዕራብ ሩሲያ በኩል በምትገኘው ኩርስክ ግዛት የተለያዩ ቦታዎችን ተቆጣጥራለች።

ሩሲያ የዩክሬንን ጥቃት በምዕራባውያን ሀገራት ድጋፍ የተደረገብኝ ነው በሚል ጉዳዩ ወደ ሦስተኛው የዓለም ጦርነት ሊያመራ ይችላል ስትል አስጠንቅቃለች።

# ቦሎቻ-የከንባታ ብሔረሰብ ባሕላዊ የጋብቻ ስነስርዓት

**ኃይሉ ሣህለድንግል**

የበርካታ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መገኛ የሆነችው ኢትዮጵያ አያሌ ባሕላዊ እሴቶች አሏት። ከእነዚህ እሴቶች መካከል ባሕላዊ የጋብቻ ስነስርዓቶች ይጠቀሳሉ። ሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች መገለጫቸው የሆነ የራሳቸው ባሕላዊ የጋብቻ ስነስርዓት አላቸው። ባሕላዊ የጋብቻ ስነስርዓቶቹ የየብሔረሰቡ ብቻም ሳይሆኑ የሀገሪቱም ብቸኛ መገለጫዎች ናቸው።

የጋብቻ ስነስርዓቶቹ ከብሔር ብሔረሰብ ሊለያዩ ይችላሉ፤ በጋብቻ ስነስርዓቱ የሚስተዋሉ የማጨት፣ ሽምግልና የመላክ፣ መሰረግ፣ መልስና ቅልቅል ማድረግ፣ ወዘተ. በየራሳቸው ሰፊ ስነስርዓት ያላቸው የሀገር እሴቶች ናቸው።

ከእነዚህ አያሌ የብሔር ብሔረሰቦች የጋብቻ ስነስርዓቶች መካከል የከምባታ ብሔረሰብ ባሕላዊ የጋብቻ ስነስርዓት አንዱ ነው። የብሔረሰቡን ባሕላዊ የጋብቻ ስነስርዓት /ቦሎቻን/ በተመለከተ በርካታ የጽሁፍ መረጃዎች እንዳሉ የዞኑ ባሕልና ቱሪዝም መምሪያ የባሕል ታሪክ ቅርስ ጥናትና ልማት ዋና የስራ ሂደት ቡድን መሪ አቶ ደስታ ዘለቀ ይገልጻሉ። ለዚህ ጽሁፍ ግን በአቶ ፈለቀ ብርሃኔ አዘጋጅነትና አሳታሚነት ‹ከምባታነት እሴቶቹ፣ ትምህርትና ልማት በሚል ርእስ ከተጻፈው መጽሀፍ ጋብቻን በሚመለከት የሰፈረውን መረጃ አቶ ደስታ አድርሰውናል። በብሔረሰቡ ዘንድ ሰርግ ‹‹ቦሎቻ›› ተብሎ እንደሚጠራ አቶ ደስታ አስታውቀዋል።

የአዲሱ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል አንዱ ዞን በሆነው የከምባታ ዞን የሚኖረው የከምባታ ብሔረሰብ ጋብቻን የሚያስተሳስረው ከራሱ ጎሳ ጋር ሳይሆን ከሌላውም ጋር መሆኑን መረጃው አመልክቷል።

በመረጃው ላይ እንደሰፈረው፤ በከምባታ ብሔረሰብ ዘንድ ጋብቻን በተመለከተ የዘር ሀረግን እስከ ሰባት መቁጠር ተለምዷል። የዘር ሀረግ ከሰባት በላይ ሲሆን በጋብቻ መጣመርን አይቃወምም፤ ምንም ይሁን ምን ከጎሳው ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያለው ወይም ያላት ማግባት አይደገፍም።

በጥንተ ከንባታ ሕዝብ ዘንድ ጋብቻ የሚመሰረተው በአብዛኛው በወላጆች ምርጫ ነው። ቤተሰብ የራሱን ጎሳ ሀረግ ከፈተሸ በሁዋላ ይመጥነናል የሚለውን ጎሳ እና የኑሮ ደረጃን ከግምት ውስጥ በማስገባት ለልጁ ትዳር ያፈላልጋል። በፍለጋው ሂደት ዘመድም ድርሻ አለው። የምትፈለገው ልጃገረድ ስትገኝ በአገናኝነት የሚወከለው የመሀል ዘመድ ነው፤ አንዳንዴ የሚያገባው ልጅ የተመረጠችውን ልጅ በድንገት ቤቷ ሄዶ እንዲያያት የሚደረግበት አጋጣሚ ቢኖርም፣ በአብዛኛው በጥንተ ከምባታ ሕዝብ ዘንድ ተጣማሪዎች የሚተያዩት በሰርጋቸው እለት ነው።

ሆኖም ተጋቢዎቹ ፈቃደኝነታቸው እንደሚጠየቅ መረጃው ጠቁሞ፣ ካልተስማሙ የሚፈርስበት ሁኔታ እንዳለም አመልክቷል። መረጃው እንደጠቆመው፤ ቤተሰብ ከውሳኔ ላይ ሲደርስ ሽማግሌዎች ተልከው በትዳር ለመዛመድና ልጃቸውን እንዲድሩ የመጠየቅ ባሕል በጥንት ከምባታዎች ዘንድ የተመለደ ነው። ሽማግሌዎቹ ወደ ሴቲቱ ቤተሰብ ሲሄዱ ስለመጡበት ጉዳይ በተዘዋዋሪ ያስረዳሉ። ቤተሰቡም በነገሩ ላይ ለማሰብ ጊዜ ይጠይቃል፤ መግደርደርም ተለምዷል።

የልጅቷ ቤተሰቦች ሽማግሌ ሲላክባቸው ወዲያውኑ ምላሽ አይሰጡም፤ ለሌላ ጊዜ ይቀጥራሉ። ይህም የሚደረገው ለትዳር የጠየቀው ቤተሰብ ምን አይነት ጎሳ እንደሆነ፤ የትዳር ጠያቂው ባህርይ፣ ስለ ቤተሰቡ ሀብት፣ ስለዝናቸውና ስለመሳሰሉት መረጃ ለማሰባሰብ እና ለማጣራት ሲባል ነው። በተሰጠው ቀነ ቀጠሮ መሰረት ሽማግሌዎች ለትዳር ከምትፈለገው ልጅ ቤተሰብ ቤት ገብተው ሲቀመጡ ጋያ እንዲያጤሱ የልጅቷ ቤተሰቦች ከሰጧቸው የመስማማታቸው አንዱ ምልክት መሆኑን ገለጹላቸው ማለት ነው፤ ሽማግሌዎቹም በባሕሉ መሰረት ይዘው የመጡትን ለምለም ሳር በእናት እጅ በማድረግ የወላጆችን ጉልበት እና ትከሻ ስመው ይቀመጣሉ።

መረጃው እንደጠቆመው፤ ቀጣዩ ሂደት ጥሎሽ የሚሰጥበት ነው፤ ይህም የቃል ማሰሪያ ቀን/ አንገተ ሱንቂ በሪ (የእጅ መሳሚያ ቀን) / መቁረጥና የጋብቻ ስነ ስርዓት የሚፈጸምበት ቀን የሚወሰንበት ነው። ጥሎሽ በከምባትኛ ቋንቋ ‹‹ቆታ›› በሚል ይጠራል፤ ጥሎሽ በእጮኛው ቤተሰብ አና በእጮኛዋ ቤተሰብ መካከል በሽማግሌዎች አማካይነት የሚቀርብ ነው።

ለምትታጨዋ ቤተሰብ ወደፊት ለሚደረገው የሰርግ ድግስ እገዛ የሚደረግ ሲሆን፣ የልጅቷ ቤተሰብ ሙሽሪት አግብታ ወደ ትዳሯ ስትሄድ ከወላጆቿ ስጦታዎች ይበረከትላታል። ጥሎሹ ከአቅም አንጻር ይወሰናል።

በጥንተ ከምባታ ባሕል መሰረት አባት ‹‹ቆላ››፣ እናት ‹‹ቂጣና ላንዳ›› ለብሰው ጊደርና ወይፈን በስጦታ ሲያበረክቱ ‹‹ዌቴቾ›› /የማጥንት እንጨት/ የማበርከት ስነ ስርዓትም ይካሄድ ነበር። ‹‹ዌቴቾ ›› የሚሰጠው ጥሩ መዓዛ ያለው እጽ በመሆኑ፣ ትርጉሙም ሙሽሮች የትዳር ሕይወታቸው ሁልጊዜ በደስታ የታጀበ እንዲሆን መመኘትን የሚያመለክት ነው።

የከብት ስጦታ/ ጌጊያ/ ም ይደረጋል። ይህ የሚደረገው መተዳደሪያቸውን ለመደጎም ሲሆን፣ ጥሎሽ ሲሰጥ መደራደርም ያለ ነው። ጥሎሹን ላመጡት ሽማግሌዎች መጠነኛ ድግስ ተዘጋጅቶ ግብዣ ይደረግላቸዋል። በወላጆች አማካይነት የሚደረገው ይህን አይነት የማጣመር ሂደት በከምባትኛ ቋንቋ ‹‹ቆርሲሻ›› በመባል ይታወቃል ሲል መረጃው ያመለክታል።

የጥንተ የከምባታ የሰርግ ስነ ስርዓት ብዙ ታዳሚ የሚገኝበት ሳይሆን፣ ከሁለቱ ቤሰቦች ውስን ቁጥር የሚሳተፍበት ነበር። ከሰርጉ አስራ አምስት ቀናት በፊት ጀምሮ በሙሽራው ቤት እየዘፈኑ ስራ ማገዝ የስነ ስርዓቱ አካል ተደርጎ ይታያል፤ በዚህም ወንዶች ጌሾና የመሳሰሉትን ይወቅጣሉ፤፣ ልጃገረዶች ደግሞ በባሕላዊ ወፍጮ እህል ይፈጫሉ። ይሄኔም ‹‹ መለሴ አኩምቦዳ፤ ወዘነ ዘርቱምቦዳ፣ ወልሴ ዶሬኖ›› / ልዩ ባለሙያ ወይም ልባም ካልሆነች፣ በሌላይቱ ትቀየራለች/ እያሉ ሙሽሪት የተስተካከለ ቁመና፣ ቁንጅናና ክህሎት እንዲኖራት በዘፈን አማካይነት ይጠቁማሉ።

ለሙሽሪት አባት የተሰጠውን የእጅ መንሻና ጥሎሽ ቁጥር በመናገር የሙሽሪትን ቤተሰብ በአሽሙር መልክ በዘፈን የመወረፍ ልምድም እንደነበር መጽሀፉ አስፍሯል። ከስንኞቹ መካከል ‹‹ መጠር ቱምቤእጋ መጨተ ሀራሩ፤ መገሬ ጎቲገ መንጋጋሙ / ኤበሉ/ ፣ መጭአች አጉር ፣ መሀ በርግ ሶሀኖ›› እያሉ ያሾፋሉ። የሙሽሪት ቤተሰቦች በበኩላቸው ሙሽሪትን ለመውሰድ የመጡትን አጃቢዎች ‹‹ ፌሶ ፌሶ ሚነኖ፣ ፊሴሬካ መጠኖ፣ ገስሙንኩስ ሀዋንቼ /ኤበሉ/፣ ጋሎ ቲሚ የራንቹ፣ ዜማ አሱተ ሶሀኖ›› እያሉ ክፉኛ እንደሚያብጠለጥሏቸውም ተብራርቷል።

በመረጃው እንደተመለከተው፤ ጥንተ ከምባታ ለሰርግ ድግስ በዋናነት የሚያዘጋጀው ምግብ ቆጮ፣ የጎመን ጮባሮ እና ከቡእላ የሚዘጋጀውን ሙቾና አይብ ናቸው። መጠጡ ደግሞ ሱሱጎና ጩሙቶ/ ቦርዴ/ ናቸው። በስጦታ መልክ ‹‹ ጌጊያ›› የሚሰጠው ጊደር፣ ወይፈን፣ ጅባ፣ ቅቤ፣ ወዳሬ፣ ቄጣ፣ ኢትሌ፣ ላንዳ፣ ልዩ ልዩ ስፌት እቃዎች፣ አንደ ወንሾሾ ደጉዴ፣ ሜሜ፣ ሁፎ፣ ሙታ፣ መሬት እና ፈረስ እንደ ገጸበረከት ሊሰጡ ከሚችሉት መካከል ናቸው። ተጨማሪ ስጦታ እንዲሰጥ ሰርገኛው እና ዘፋኞች ሲገፋፉ ቤተሰብ መልስ ሊሰጥ ‹‹ቡላ ኮሪን፣ ባዮ ሱሉሙታ ቆንቴም›› በቅሎን ከነኮርቻው፣ ቦቃ ጊደርን ሸልመናል/ ብሎ መልስ ይሰጣል። በመጨረሻም ወላጆች ምርቃታቸውን ይሰጣሉ።

ሙሹሪት በምትሸኝበት ወቅት የመፎጋገር እና በሽሙጥ መነካካት የነበረ ሲሆን፣ ዘፈን ግን እስከዚህም የጎላ አልነበረም። በጥንተ ከምባታ ባሕል ልጃገረድ ተድራ ስትወጣ አግቢው ወዳሬ /የቆዳ ውጤት/ ለብሶ ነው። ስልጣኔ እያሰፋ ሲሄድ ‹‹ባልቶ›› ይዞ መጥቶ ማልበስ የባህሉ አንዱ ክፍል ነው። ሙሽሪትን ለመውሰድ የመጡ ሰርገኞችም ወደ ቤት እንዲገቡ ከተፈቀደ በኋላ ቤተሰብ ሙሽሪትን ከመስጠቱ በፊት በወደፊት ሕይወቷ ኃላፊነት የሚወስድ ሽማግሌ ተለይቶ እንዲታወቅ ጥያቄ ያቀርባል።

በአደራ መልክ ኃላፊነቱን የሚወስደው ሽማግሌ ተግባር ተጣማሪያን በኑሯቸው የሀሳብ ግጭት እና ነገሮች ሲወሳሰቡ ችግሮችን መፍታት ነው። ሽማግሌው ተለይቶ ከታወቀ በሁዋላ ሙሽሪት ወደ ውጭ ከመውጣቷ በፊት ቅቤ ተቀብታ ወደ ደጃፍ ወጥታ በወላጆቿ በእህቶቿ በወንድሞቿ በቅርብ ዘመዶቿ እና በሽማግሌዎች ከተመረቀች በሁዋላ የሁሉንም እጆች መዳፍ ትስማለች። ከምባታ ሴት ልጁን ለትዳር አውጥቶ ሲሰጥ ክፉ ነገር ሲደርስባት ከባል ሌላ በጉዳዩ ዙሪያ ኃላፊነት የሚወስድ ግለሰብ ተለይቶ እንዲሰጥ ያደረገበት ባሕላዊ አርቆ አሳቢነት እጅግ የሚደነቅ ነው።

ዱሮ አጃቢዎች ሙሽሪትን ለመውሰድ የሚመጡት በእግር ነበር፤ ሚዜዎቹ እና አጃቢዎቹ ሙሽሪትን በትከሻቸው ተራ በተራ በመሸከም ይወስዷት ነበር። ይህ ግን በሂደት በጋማ ከብት ተተካ። ሙሽሪት ከሚዜዎቿ ጋር ወደ ሙሽራው ቤት የምትወሰደው በጭፈራ ታጅባም ነበር። በጋማ ከብት ጀርባ ላይ ተቀምጣ ስትሄድ በተለይ በበቅሎ ላይ ከሆነ ሙሽራው ቤት ስትደርስ የእንሰት ቅጠል በባዝራ ጀርባ ላይ ተደርጎ ለአፍታ ተቀምጣ እንድትወርድ ይደረጋል። የዚህ ስነ ስርዓት ዋና መልእክት ሙሽሪት ፍሬያማ እንድትሆን ማሰብን ያመለክታል ሲል መረጃው ጠቁሟል።

በመረጃው እንደተመለከተው፤ ከጋማ ከብት ጀርባ ስትወርድ ከደጃፍ ላይ ጅባ ተነጥፎላት በተዘጋጀው ቦታ ትቀመጣለች። ሁለት ሕጻናት ወንድና ሴት በሁለቱ ጭኖቿ ላይ እንዲቀመጡ ይደረጋል። የዚህ ስነ ስርዓት ዋና ትርጉምም ሙሽሪት ከአብራኳ በሚገኘው ፍሬ እንድትንበሸበሽ መልካም ምኞት ለመግለጽ ነው።

አማቷ አዲስ ስም ታወጣላታለች። ከሙሽሪት ወላጆች ቤት የተሰጣት ንብረት አንድ በአንድ ርክክብ ይደረጋል። ይህ ስነ ስርዓት ተከናውኖ እንዳበቃ ሙሽሪት በሚዜ ታዝላ፣ በአጃቢዎች ተከባ ወደ ተዘጋጀላት እልፍኝ ትወሰዳለች። ይሄ ደግሞ የሙሽራው እህቶች በር ዘግተው በመያዝ ስጦታ እንዲሰጣቸው መጠየቃቸውን ይያያዙታል። ስጦታ ለመስጠት ቃል ይገባናም ሙሽሪት ወደ እልፍኝ እንድትገባ ይደረግና በተዘጋጀው ቦታ የጫጉላ ጊዜዋን ታሳልፋለች።

ለአማቾቿ ክብር ስትልም የጫጉላ ጊዜዋን ብትጨርስም፣ እስከምትወልድ ድረስ በይፋ ፊቷን አታሳይም። ወልዳ ከተመረቀችና የባል ቤተሰብም ስጦታ ሰጥቷቸው የራሳቸውን ጎጆ ቀልሰው መኖር ሲጀምሩ ባህሉ መሰረት ተጥሎባት የነበረው የመሸፋፈኑና በይፋ ያለመታየት ገደብ ያበቃና ማኅበራዊ ሕይወት ትጀምራለች።

መልስ ‹‹ ምንአግሽ›› የመጥራት ባሕል ያለ ሲሆን፣ ይህ ልምድ የቤተሰብ ዝምድናን ለማጎልበት፣ ትውውቁን ለማጠናከር፣ እርስ በርስ መዛመድን በጥልቅ ለማሳየት እና አቅምን ለማሳየት የሚደረግ ስነ ስርዓት ነው። በዘመኑ በዋናነት የሚቀርበው ግብዣ ቆጮ ከአይብ ጋር ሲሆን፣ መጠጡ ሱሱጎና ጩሙቶ ነው። በሂደት በሬና በግ እየታረደ የመስተንግዶው አንድ አካል ሆነ።

በጥንተ ከምባታ ዘንድ በሽማግሌ ከሚጠየቅ እና በቤተሰብ አማካይነት ከሚቀነባበር መተጫጨት በተጨማሪ ‹‹ሜዱ›› /ጠለፋ/ እና ‹‹ሄራሙ›› በልጃገረድ ስምምነት የሚደረግ የትዳር ጥምረት እንደነበር መረጃው ያስታውሳል። ጠለፋ እና በልጃገረዷ ስምምነት የመጣመር አካሄድ በቤተሰብ ደረጃ ብዙ የማይደገፍ ቢሆንም፣ በባሕሉ ውስጥ ነበር። በተለይ ልጃገረድ በራሷ ፈቃድና ስምምነት በውዴታ የምታደርገው ትዳር ከገዛ ቤተሰቧም ጋር የሚያጋጭ አንዳንዴም እስከ መረገም ሊያደርስ የሚችል ነው።

ጠለፋ በተለይ በጠላፊው እና በተጠላፊዋ ቤተሰብ መካከል ወደ ጠላትነት ተቀይሮ በጉዳዩ ላይ ከቤተሰብ በተጨማሪ በጎሳዎች መካከል ወደለየለት መቃቃር እና ደም እስከመቃባት ሊያደርስ ይችላል። አንዳንድ ጽንፈኛ ቤተሰብ ተጠላፊዋ ብትወልድ እንኳ እስከማለያየት የሚያደርደስበት አጋጣሚም ሲከሰት ተስተውሏል። ጠለፋ /ሚዱ/ ሆነ በማባበልና በማግባባት /ሄራንቻ/ የተደረገ ጋብቻ የቤተሰብ ሚና የሌለው ቢሆንም፣ በአገሬው ሽማግሌ የማግባባትና የማብረድ ጥረት እርቅና ሰላም በቤተሰቦች መካከል እንዲወርድ የሚደረግበት ሁኔታም አለ። ይህም ባሕላዊ የእርቅ ሂደት ከምባቶች ነገሮችን በጥሞና የመፍታት ብቃታቸውን በይበልጥ ያሳያል።

በከምባታ ባሕል ብዙ ሚስት ማግባት በጣም የተስፋፋ አልነበረም። ሆኖም ግን ባል ሲሞት፣ የሟቹን ሚስት ወንድም አልያም የቅርብ ቤተሰብ ‹‹ ረጊታ ›› /ውርስ/ ማግባት በተወሰነ ደረጃ ይፈጸም ነበር። ከምባታ የዚህን አይነት ባሕል ያዳበረው ለሟች ልጆችና ሚስት ከማሰብ በመነጨ መሆኑን መረጃው ይገልጻል። ከዚህ በተጨማሪም ሟች ያፈራው ንብረት ወደ ባዳ እጅ እንዳይገባ ለመከላከልም ጭምር መሆኑን ያመለክታል። ሁለት ሚስት የማግባት ሁኔታ በአንዳንድ አጋጣሚዎች፣ ከእምነት፣ ከሀብትና ከማኅበራዊ ሕይወት ጋር ተያይዞ የሚደረግበት ሁኔታ እንዳለም ተጠቁሟል።

ዛሬ ትዳር የመመስረቱ ሁኔታ በሁለቱ ተጣማሪያን መካከል እየተደረገ ወደ ዘመናዊነት እየተሸጋገረ እንደሆነ የጊዜው ነባራዊ ሁኔታ ያሳያል። ወደ ዘመናዊነት መቀየሩ የሚያስከፋ አይሆንም። ዋና ነገሩ አዲሱ ዘመናዊ የመተጫጨት እና የመጋባት ሁኔታ ምን ያህል የአባቶችን ወግ እና ባሕል ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው የሚለው ነጥብ ከጥቅሙ እና ከጉዳቱ አኳያ ተያይዞ ቢታይ መልካም ይሆናል። አንድ ነገር ዘመነ ማለት ፍጹም ሆነ ሳይሆን ተግዳሮትም አብሮት እንደሚመጣ መዘንጋት የለበትም። ጥሩ እና መልካም ባሕል ከዘመኑ ጋር እንዲሄድ ቢደረግ የከምባታ የትዳር ባሕልና እሴት ተጠብቆ ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ ይረዳል የሚል እምነት እንዳለም በመረጃው ተጠቁሟል።

> **በጥንተ ከምባታ ባሕል መሰረት አባት ቆላ፣ እናት ቂጣና ላንዳለብሰው ጊደርና ወይፈን በስጦታ ሲያበረክቱ ዌቴቾ/ የማጥንት እንጨት/ የማበርከት ስነ ስርዓትም ይካሄድ ነበር። ዌቴቾ የሚሰጠው ጥሩ መዓዛ ያለው እጽ በመሆኑ ሲሆን፣ ትርጉሙም ሙሽሮች የትዳር ሕይወታቸው ሁልጊዜ በደስታ የታጀበ እንዲሆን መመኘትን የሚያመለክት ነው**

# የሶማሊያ ወቅታዊ ሁኔታ እና በአካባቢው ያንዣበበው አደጋ

**እስማኤል አረቦ**

አደጋ ያንዣበበበት የአፍሪካ ቀንድ በሚለው መጽሃፋቸው ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ሶማሊያን እንዲህ ይገልጿታል። የሶማሊያ ታሪክ የሚያስደንቅም፤ የሚያሳዝንም ነው። በመሰረቱ ሶማሊያ ሳይጸነስ የተወለደ ሀገር ነው።

ሶማሊላንድ እኤአ በሰኔ 26 ቀን 1960 ከእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ነጻ ወጥታ ራሷን ስትችል በደቡብ በኩል የኢጣሊያ ግዛት የነበረችው ሶማሊያም ለአስር ዓመታት ያህል በኢጣሊያ ስር የተባበሩት መንግስታት የሞግዚት አስተዳደር ሆኖ ቆይታ ሀምሌ 1ቀን 1960 ነጻነቷን አገኘች።

ሆኖም የተለያየ የአስተዳደር ብሂልና አካሄድ የነበራቸው ሶማሊላንድና ዋናዋ ሶማሊ ያለምንም ምክክር እና መግባባት እንዲዋሃዱ ተደረገ። ይህም ቅራኔ ፈጠረ። በተለያዩ ጎሳዎች መካከልም በሚኖር ሽኩቻ በመኖርና ባለመኖር መሃል የሚቃትት ሀገር ሆኗል። » ሲሉ ሀገሪቱ የቆመችበት መሰረት የረጋ አለመሆኑን ያብራራሉ።

በአጠቃላይም ሶማሊያ ከመመስረቻዋ ጀምሮ ያልጸናች በመሆኑም ዘወትር ግጭትና ሁከት አጥቷት አያውቅም። ይህም ሁኔታ ለአሸባሪዎችና ሰርጎገቦች ምቹ ሁኔታ ከመፍጠሩም ባሻገር አካባቢው በግጭትና በአለመረጋጋት እንዲታወቅ አድርጎታል።

ሶማሊያ ባለመረጋጋትና በግጭት ውስጥ የምትኖር ሀገር ነች። ከዚያም አልፎ መንግሥት አልባ ሆና ዘመናትን ተሻግራለች። በእነዚህ የመከራ ዓመታት ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሶማሊያ ሕዝብ ጎን ተለይቶ አያውቅም።

በፊት 'AMISOM' አሁን ደግሞ 'ATMIS' እየተባለ በሚጠራው የአፍረካ ኅብረት የሶማሊያ ሰላም ማስከበር ተልዕኮ በኩል ኢትዮጵያ ለሶማሊያ ሰላም ጉልህ አስተዋጽኦ ስታደርግ ቆይታለች። በዚህ ተልዕኮም አብዛኛውን የሶማሊያ መሬት በመሸፈንና ከጥቃት በመከላከል የሶማሊያ ሕዝብ በሰላም ወጥቶ እንዲገባ፤ የሶማሊያ መንግስትም ተረጋግቶ መንግስታዊ ስራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል።

በአንድ ወቅት የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ እንደተናገሩት፤ 60 በመቶ የሚሆነውን የሶማሊያ ክፍል የሚጠብቀውና ከአልሻባብ ጥቃት የሚከላከለው የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ነው።

ኢትዮጵያ በሶማሊያ ጠንካራ መንግሥት እንዲፈጠር መስዋዕትነት ስትከፍል ቆይታለች። አልሻባብ የሁለቱም የጋራ ጠላት መሆኑ ደግሞ ሁለቱ ሀገራት በጋራ እንዲቆሙ ያስገደደም ነበር።

የኢትዮጵያን የሶማሊያ ግንኙነት ከዚህም በላይ ነው። የሁለቱ አገሮች ሕዝቦች በሁለት አገሮች የሚኖሩ አንድ ሕዝቦች ናቸው። ዕጣ ፈንታቸው የተሳሰረ ነው። ወደ 16 ሚሊዮን ሕዝብ ያላት ሶማሊያ እ.ኤ.አ. በ2020 ወደ 294 ሚሊዮን ዶላር የሚገመት ሸቀጣ ሸቀጥ ከኢትዮጵያ አስገብታለች። የንግድ ልውውጡም እያደገ እንደሚሄድ ይታመናል።

አሁን ያለው የሶማሊያ መንግስት ይህን ሁሉ የተመለከተ አይመስልም። ጭራሹኑ ለኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላት የሆኑ ሀገራትን ጭምር በሰላም አስከባሪነት ስም ጋብዞ ወደ ሶማሊያ እንዲገቡ እያደረገ ነው። ይህ ደግሞ ለኢትዮጵያ ብሎም ለአፍሪካ ቀንድ አዲስ ስጋት ይዞ መጥቷል።

የጉዳዩን አሳሳቢነት አስመልክቶ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባወጣው መግለጫም በሶማሊያ የአፍሪካ ሕብረት የሽግግር ተልዕኮ (አትሚስ) በቀጣይ የሚኖረው አዲስ የሰላም ተልዕኮ አወቃቀር ሁኔታ በአፍሪካ ቀንድ ቀጣና ላይ አዲስ ስጋት ይዞ መምጣቱ ኢትዮጵያን የሚያሳስብ ሆኗል።

የአፍሪካ ሕብረት እና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ለዚሁ አዲስ ሽግግር እየተዘጋጁ ባሉበት ወቅት ቀጣናው ሊተነበይ ወደማይቻል ፈተና ውስጥ እየገባ ይገኛል። ሌሎች ተዋናዮች የአፍሪካ ቀንድ ክልልን ለማተራመስ እርምጃ ሲወስዱ ኢትዮጵያ በዝምታ አትመለከትም ሲል የሁኔታውን አሳሳቢነት ያብራራል።

**ዘይላ ሶማሊያ እንደ ሀገር ከመፈጠሯ በፊት ኢትዮጵያ የምትጠቀምበት የባሕር በር ነው። ከዛግዌ መንግሥት ጀምሮ ኢትዮጵያ በወደቡ ስትጠቀም ኖራለች። ለኢትዮጵያ ቅርበት አለው። ከሞቃዲሾ በርካታ ኪሎ ሜትሮችን የሚርቅ ስለሆነ ሶማሊያ ልትጠቀምበት አትችልም። ስለዚህም መነጋገር ከተቻለ በቅርብ ርቀት ላይ የሚገኘውን የዘይላን ወደብ ኢትዮጵያ ብትጠቀምበትና ሶማሊያም በምትኩ ጥቅም ብታገኝ ሁለቱም ሀገራት አሸናፊ መሆን ይችላሉ**

በአጠቃላይ ሶማሊያ የመረጠችው መንገድ በምስራቅ አፍሪካ ቀጣና ብዙ መዘዝ ይዞ የሚመጣ ነው። በመጀመሪያ ኢትዮጵያ ለሶማሊያ ሕዝብ የከፈለችውን መስዋዕትነት ከንቱ የሚያስቀርና ለሶማሊያ ሰላምና መረጋጋት የተከፈለውንም የሕይወት ዋጋ ጭምር ዋጋ የሚያሳጣ ነው።

በሌላም በኩል በኢትዮጵያ ሰራዊት የሕይወት መስዋዕትነት ጭምር ተመናምነው የነበሩት የአልሸባብና የአልቃኢዳ ኃይሎች እንደገና እንዲያንሰራሩና አካባቢውን የሽብር ማዕከል እንዲሆን በር የሚከፍት ነው። ይህ ደግሞ ስጋቱ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለዓለም ሕዝብ ጭምር ነው።

የሶማሊያ መንግሥት እየሄደበት ያለውን መንገድ ማጤን ይኖርበታል። በተለይም ለውዝግቡ መነሻ ተደርጎ የሚወሰደውን የባሕር በር ጥያቄ የሶማሊ ሕዝብም ሆነ የቀጣናው ሀገራት ሊረዱት ይገባል። የኢትዮጵያ መንግሥት ወደብና የባሕር በር ለኢትዮጵያ ወሳኝ መሆኑንና የጎረቤት ሀገራትም ኢትጵያን እንዲተባበሯት ተደጋጋሚ ጥያቄ ቢያቀርብም በግልጽ የተቀበለ ሀገር የለም።

የኢትዮጵያ ወደብ አልባ መሆንም ከስነልቦናዊ ቀውስ ባሻገር ለበርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ጫና ሕዝቡ እንዲጋለጥ አድርጎታል። የኢትዮጵያን ክብርና ዝና ዝቅ እንዲል ከማድረጉም ባሻገር በኢኮኖሚ ረገድም ተጎጂ እንድትሆን አድርጓታል። ለበርካታ መሰረተ ልማቶችና ለድህነት መቀነሻ ይውል የነበረውን ከ1ነጥብ 6 ቢሊዮን ዶላር በላይ በየዓመቱ ለወደብ ብቻ በማዋል በድህነት ውስጥ እንድትማቅቅ አድርጓታል።

ኢትዮጵያ ለሶማሊላንድ የሰጠችውን ዕድል ለሌሎች የሰጠች ቢሆንም የተጠቀመችበት ግን ሶማሊላንድ ብቻ ነች። ዋናዋ ሶማሊያም የዚህ ዕድል ተጠቃሚ የመሆን ዕድል አላት። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ሰሞኑን በፓርላማ ተገኝተው እንዳሉት ‹‹የሶማሊያ መንግሥት በአንድ ሰዓት በረራ እና በአንድ ሰዓት ውይይት ይህን ነገር መልክ ማስያዝ ይችላል። በጣም ቀላል ነገር ነው ።

ምክንያቱም ከሶማሌ መንግሥት ጋር ምንም ጸብ የለንም። የሶማሌ መንግሥት የመረጠው ግን እኛን ከማናገር በየሰፈሩ እየዞረ እኛን መክሰስ ነው። ያለኝ ምክር ብር አታባክኑ ነው። በየሀገሩ ስንሄድ፤ በጣም ብዙ ወጪ ይወጣል፤ ብር ከምናባክን እሱን ሰብስበ አድርገን አንድ ኪሎ ሜትር ዎክ ዌይ ብንሰራበት፤ አንድ ትምህርት ቤት መቋዲሾ ብንሰራበት ሕዝብ ይጠቅማል።

እኛን ለመክሰስ ሀገር ለሀገር መሄድ አያስፈልግም ። አዲስ አበባ መምጣት ይቻላል። ለመነጋገር ዝግጁ ነን። ሶማሊያ እንድትጎዳ፤ እንድትፈራርስም፤ እንድትበተንም የሚፈልግ መንግሥት አይደለም። ቢሆን ልጆቹን ልኮ አይሞቱም። የኢትዮጵያ መንግሥት ጥያቄ የባሕር በር ጥያቄ ነው። ይሔ ሕጋዊ ጥያቄ ነው። ይሄን በሰላማዊ እና በንግግር መልኩ እንደማንኛውም ኮሚዲቲ/ ሸቀጥ ለመቀበል ኢትዮጵያ ዝግጁ ነች።

ለምሳሌ ወይ ሶማሌ፤ ወይ ጅቡቲ ወይም ሌሎቹ፤ የባህር በር አላቸው፤ ግን እንደ ኢትዮጵያ ሊያመርቱ አይችሉም። እኛ የተሻለ መሬት አለን፤ የተሻለ ውሀ አለን፤ ኢነርጂ ምግብም፤ ከኛ አቦካዶ ከነሱ ውሀውን ብንጋራ ምንም ችግር የለውም። ንግድ ነው።

ተጠቅመው ተጠቅመን አድገው አድገን፤ ተባብረን አብረን ብንሄድ ለሪጅኑ/ለአካባቢው ለልጆቻችንም ጠቃሚ ነው። እናንተ እንዲህ አይነት ጥያቄ አታንሱ ቢባል ግን፤ ጥያቄ አታንሱ ብለህ የምታፍነው ጉዳይ አይደለም፤ እውነት እስከሆነ ድረስ ጊዜውን ጠብቆ ይወጣል።››ሲሉ መልዕክት ማስተላለፋቸው የሚታወስ ነው።

በአሁኑ ወቅት 120 ሚሊዮን ሕዝብ በ2050 አካባቢ ደግሞ በእጥፍ የሚያድግ ሕዝብ ተይዞ "ስለቀይ ባሕር እና ስለ ወደብ አታንሳ፤ ዝም ብለህ ተቀመጥ" የሚል አፋኝ አመለካከት ሊኖር አይገባም። የሶማሊያ መንግሥት ኢትዮጵያ ከሶማሊላንድ ጋር የተፈራረመችውን የመግባቢያ ሰነድ ማክበር አሊያም ደግሞ የራሷን የባሕር በርና የወደብ አማራጮች ማክበር ይገባታል። ከሁለቱ ውጭ መሆን ግን በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያውያን የሚቀበሉት አይደለም።

ሶማሊያ በሺዎች ኪሎ ሜትር የሚቆጠር የባሕር በር አላት። ግን ይህ ሁሉ ኪሎ ሜትር ለሶማሊያ ወደብ ሆኖ ሊያገለግል የሚችል አይደለም። ስለዚህም ሶማሊያ ከኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ተጠቃሚ ለመሆን ከፈለገች ወደብ ከኢትዮጵያ ጋር ማልማት ትችላለች። ወይንም ደግሞ ለም መሬት ወስዳ በምትኩ ወደብ ልታቀርብልን ትችላለች። ብቻ አማራጩ ብዙ ነው።

ዘይላ ሶማሊያ እንደ ሀገር ከመፈጠሯ በፊት ኢትዮጵያ የምትጠቀምበት የባሕር በር ነው። ከዛግዌ መንግሥት ጀምሮ ኢትዮጵያ በወደቡ ስትጠቀም ኖራለች። ለኢትዮጵያ ቅርበት አለው። ከሞቃዲሾ በርካታ ኪሎ ሜትሮችን የሚርቅ ስለሆነ ሶማሊያ ልትጠቀምበት አትችልም። ስለዚህም መነጋገር ከተቻለ በቅርብ ርቀት ላይ የሚገኘውን የዘይላን ወደብ ኢትዮጵያ ብትጠቀምበትና ሶማሊያም በምትኩ ጥቅም ብታገኝ ሁለቱም ሀገራት አሸናፊ መሆን ይችላሉ።

ከዚህ በተረፈ ግን የኢትዮጵያን ፍላጎት አፍኖ አሸናፊ መሆን አይቻልም። ለሶማሊያ ሕዝብ በርካታ ውለታ ለዋለችው ኢትዮጵያ በየስፍራው እየዞሩ ስም ማጥፋትና በኢትዮጵያ ላይ ሀገራት የተሳሳተ አቋም እንዲይዙ ለማድረግ የሚደረገው ጥረት የኢትዮጵያን ውለታ የዘነጋ ነው።

የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ለሶማሊያ ሰላም ሲል ሕይወቱን ከመገበሩም በሻገር እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ2008 የሶማሊያ መንግሥት ሲቋቋም ቀድማ ኤምባሲ የከፈተችና ዕውቅና የሰጠችው ኢትዮጵያ ናት። በተለያዩ ጊዜያትም በሶማሊያ ሰው ሰራሽና ተፈጥሮ አደጋዎች ሲያጋጥሙ የሶማሊያ ሕዝብን በሯን ከፍታ የምትቀበለው ኢትዮጵያ ብቻ ነች። ታዲያ ይህንን ሁሉ ውለታ ለምትውለው ኢትዮጵያ የሶማሊያ መንግሥት በተቃራኒው እየሰራ ያለው ኢትዮጵያን የማጠልሸት እና በኢትዮጵያ ላይ ስጋት የሚደቅን እርምጃ መውሰድ ጉዳዩን እንቆቅልሽ ያደርገዋል።

በተለይም በሰላም አስከባሪ ስም የኢትዮጵያን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥሉ ተግባራትን ለመፈጸም መሞከሯ የቀጣናውን ችግሮች ከማባባስ ባሻገር ይዞ የሚመጣው አንዳችም መፍትሄ የለም። በአንድ ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በፓርላማ ተገኝተው እንደተናገሩት ፤ የሶማሊያን ሕዝብ ለመታደግ ሲባል ኢትዮጵያ በሺዎች የሚቆጠሩ ወታደሮቿን አጥታለች።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት፤ የሶማሌያ ሕዝብ፤ የሶማሌያ ጎሳዎች በአብዛኛው በእኛ ውስጥ ስላሉ ጎረቤት ብቻ ሳይሆን ወንድሞቻችን ናቸው። ለሶማሊያ ሰላም ሞተናል፤ ለሶማሊያ አንድነት ሞተናል። ለሶማሊያ ያለንን ክብር፤ ብልጽግና ከማንም መንግሥታት በላይ አሳይተናል።

ሶማሊያን እንደ ኢትዮጵያዊ ቆጥረን የደገፍነው እኛ ነን። በሶማሌያ አንድነት የኢትዮጵያ መንግሥት ጥያቄ የለውም። በኛ እና በሶማሌላንድ መካከል የተደረገው የመግባቢያ ስምምነት ለሁሉም ጎረቤቶቻችን ያቀረብነው ጥያቄ፤ ሁሉን ለምነን ጠይቀን ምላሽ ስናጣ ከመለሰልን አካል ጋር ተፈራረምን እንጂ ከሶማሊያ አንድነት ጋር የተያያዘ ጥያቄ አይደለም ብለዋል።

የሶማሊያ መንግሥት ይህን ሁሉ በመዘንጋት ወይም ኢትዮጵያ ውለታ ፊቱን በማዞር ከኢትዮጵያ ጠላቶች ጋር አብሮ እየሰራ ነው። ከዚያም አልፎ የኢትዮጵያን ታሪካዊ ጠላቶች ወደ ግዛቱ ጋብዟል። ይህ ደግሞ አልሸባብ እንደገና እንዲያንሰራራ እና የሶማሊያ ሕዝብ ዳግሞ ለስቃይ እንዲዳረግ መፍቀድ ነው። ከዚህም አልፎ የምስራቅ አፍሪካ ቀጣና የአሸባሪዎች መናኸሪያ እንዲሆን በማድረግ የበለጠ የግጭትና የጦርነት ቀጣና እንዲሆን በር መክፈት ነው።

# ስፖርት

## የንግድ ባንክ ሴቶች ቡድን የሴካፋ ዋንጫ አሸናፊ ሆነ

ዓለማየሁ ግዛው

የሴካፋ ዞን የሴቶች ሻምፒዮንስ ሊግ ውድድር ባለፉት አራት ዓመታት ሲካሄድ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሦስት ጊዜ የፍፃሜ ተፋላሚ ቢሆንም በሁለቱ ዋንጫ ማሳካት አልቻለም ነበር። ዘንድሮ ግን ለሦስተኛ ጊዜ የፍፃሜ ተፋላሚ ሆኖ በቀረበበት ፍልሚያ የዞኑን ዋንጫ በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ ለማንሳት በቅቷል።

ለአራተኛ ጊዜ ከነሐሴ 11 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ አስተናጋጅነት ሲካሄድ የቆየው የሴካፋ ዞን የሴቶች ሻምፒዮንስ ሊግ የማጣሪያ ውድድር ትናንት በአዲስ አበባ አበበ ቢቂላ ስቴዲየም ተጠናቋል። በፍፃሜው ፍልሚያ በሜዳውና በደጋፊው የኬንያ ፖሊስ ቡሌትን የገጠመው ንግድ ባንክ ጨዋታውን አንድ ለምንም በማሸነፍ ዋንጫውን አንስቷል።

ከማራኪ የጨዋታ ብልጫ ጋር ዋንጫውን ለማንሳት የተፎካከሩት ንግድ ባንኮች ያገኙትን የግብ አጋጣሚ መጠቀም ሳይችሉ ቢቆዩም፣ 78ኛው ደቂቃ ላይ በአስደናቂ ቅብብል በኮከቧ ሴናፍ ዋቁማ ግሩም አጨራረስ ታግዘው ኳስና መረብ አገናኝተዋል። ብቸኛዋን የማሸነፊያ ግብ ያስቆጠረችው ሴናፍ ዋቁማም በስድስት ግቦች የውድድሩ ከፍተኛ ጎል አስቆጣሪ ሆና አጠናቃለች። የአማካኝ ስፍራ ተጫዋች መሳይ ተመስገን ደግሞ የውድድሩ ኮከብ ሆና ተመርጣለች። ይህም ንግድ ባንክን በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የሴካፋን የክለቦች ዋንጫ ከማንሳት ባለፈ የሴካፋን ዞን ወክሎ የአፍሪካ ሻምፒዮንስ ሊግ




የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሴቶች ቡድን በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ የሴካፋን ዋንጫ አንስቷል፣

ተሳታፊ አድርጎታል።

የውድድሩ ኮከብ አሠልጣኝ የኬንያ ፖሊስ ቡሌትስን ለፍፃሜ ያበቃችው ቤልዲን አዴምቤ ሆና ስትመረጥ፣ ኮከብ ግብ ጠባቂም ከተመሳሳይ ክለብ ኤ ኩንዱ ተመርጣለች።

ዘጠኝ ክለቦች በሁለት ምድብ ሲፎካከሩበት በቆየው ውድድር ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሁሉንም ጨዋታዎች አሸንፎ ነበር ለፍጻሜው ፍልሚያ መብቃት የቻለው። በምድብ አንድ ሦስቱንም ጨዋታዎች በማሸነፍ ዘጠኝ ጎሎችን አስቆጥሮ ሦስት ብቻ ሲቆጠሩበት የግማሽ ፍጻሜውን ጨዋታም በሁለቱም የጨዋታ አጋማሾች አስቆጥሮም አስደናቂ ጉዞ አድርጓል።

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሴቶች እግር ኳስ ቡድን በ2013 ዓ.ም ኬንያ ባስተናገደችው የመጀመሪያው ውድድር ላይ 2ኛ፣ በ2014ቱ የታንዛኒያ ውድድር ላይ ደግሞ 3ኛ እንዲሁም በ2015 ዓ.ም ዑጋንዳ ላይ ተደርጎ በነበረው ውድድር 2ኛ ደረጃን በመያዝ ማጠናቀቁ ይታወሳል። ንግድ ባንክ በነዚህ ዓመታት በውድድሩ አስደናቂ ጉዞው የፍፃሜ ተፋላሚ ሲሆን ቡድኑን በዋና አሠልጣኝነት የመራው ብርሃኑ ግዛውም በመጨረሻም ዋንጫውን በማንሳት አዲስ ታሪክ ሠርቷል።

ክለቡ ከዚህ ቀደም እአአ በ2021 ውድድሩ በተጀመረበት የመጀመሪያ ተሳትፎ ለፍጻሜ ደርሶ ባለቀ ሰዓት በተሰጠበት የፍጹም ቅጣት ምት በኬንያው ቪጋ ክዊንስ ተሸንፎ ዋንጫውን ማንሳት እንዳልቻለ ይታወሳል። አምናም በተመሳሳይ በዑጋንዳ አስተናጋጅነት በተካሄደው ውድድር ለፍፃሜ ቀርቦ በታንዛኒያው ጂኬቲ ኩዊንስ በመለያ ምት ተሸንፎ ከዋንጫ ውጪ መሆኑ ይታወቃል።

ከፍፃሜው ጨዋታ ቀደም ብሎ ከቀኑ 5 ሰዓት ላይ በተካሄደው የደረጃ ጨዋታ የዑጋንዳው ካዌምፔ ሙስሊም ሌዲስ የታንዛኒያውን ሲምባ ኩዊንስን 2 ለ 0 በሆነ ውጤት በማሸነፍ ውድድሩን በሦስተኛነት አጠናቋል።

የሴካፋ ዞንን በመወከል በአፍሪካ ሴቶች ሻምፒዮንስ ሊግ የሚሳተፍ አንድ ቡድን ለመለየት ዘጠኝ ቡድኖች በሁለት ምድቦች ተከፍለው ውድድራቸውን ሲያደርጉ ቆይተዋል። የዋንጫው አሸናፊ ቡድንም የሴካፋን ዞን ወክሎ በ2024 የአፍሪካ ሴቶች ሻምፒዮንስ ሊግ ዋንጫ የሚሳተፍ ይሆናል። በሁሉም የአፍሪካ ዞኖች የሚገኙ የሴት ቡድኖች የማጣሪያ ውድድር ካደረጉ በኋላ ዞኖቻቸውን በመወከል የአፍሪካ ሴቶች ቻምፒዮንስ ሊግ ላይ ይካፈላሉ።